ቀን: ታህሳስ 1/2003 ዓ.ም

ይድረስ ለኢትዮጵያዊያን በሙሉ በያላችሁበት

ጉዳዩ - በወያኔ እስር ቤቶች ሞልቶ ስለፈሰሰው የወገኖቻችሁ ስቃይና ሰቆቃ እንድታውቁት

## 1. ትንሽ ስለ ራሳችን፤

በወያኔ የወንጀል ምርመራ፣ የወህኒና የእስር ቤቶች አስተዳደር አካባቢ የምንሰራ የፖሊስ፣ የፌደራልና የደህንነት ባልደረቦች ነን። ባጭሩ እንድታውቁት የምንፈልገው በሃገሪቱ እስር ቤቶችና ማእከላዊ እየተባለ በሚጠራው በአዲስ አበባ ከተማ የሚገኘውን እስር ቤት ጨምሮ ስለሚካሄደው የእስረኞችና የአሳሪዎች ግንኙነት፣ ስለእስረኞች አያያዝ፣ በእስረኞች ላይ ስለሚፈጸም ግፍና ሰቆቃ ማወቅ የምንችልበት የተወሰነ እድል ያለን ሰዎች መሆናችንን ነው። የሃገሪቱ እስር ቤቶች ስንል በይፋ ስለሚታወቁት ዋና ዋና የፌደራል መንግስቱ እስር ቤቶች ማለታችን እንጂ በወያኔ የደህንነት ሃላፊዎች በአዲስ አበባና በየክልሉ በድብቅ ሰለተመሰረቱት እስር ቤቶች ማለታችን አይደለም። ወይም በየክልሉ በየዞኑና በየወረዳው በክልል ንጉሶች ስር ስለሚተዳደሩት በሽዎች የሚቆጠሩ ማጎሪያ ጣቢያዎች አይደለም። ዛሬ በኢትዮጵያ ውስጥ የእስረኛው ብዛት ደርግ ከፍተኛ ግፍ ሲፈጽምበት ከነበረበት ከ1969 እስከ 1970 ከቆየው ዋናው የቀይ ሽብር ዘመን ጋር ሲነጻጸር በትንሹ ከ50 እጥፍ በላይ አድጓል። ይህ እየሆነ ያለው እንደደርግ ዘመን ወያኔን በከተማና በገጠር የሚፋለሙ ጠንካራ ተቃዋሚዎች በሌሉበት ሁኔታ መሆኑ ደግሞ ሁላችንንም ሊያሳስብ የሚገባ ጉዳይ ነው። በመላው ሃገሪቱ ስለተበተነ ህጋዊና (በወያኔ ህግ ማለታችን ነው) በህገወጥ መንገድ ስለታሰረ በብዙ አስር ሽዎች ስለሚቆጠር እስረኛ  እንወቅ ብንልም የምናውቅበት አቅም የለንም። ከዚህ በታች የምናቀርብላችሁ መረጃ የተሰባሰበው ራሳችን ባይናችን ካየነው፤ በጆሮአችን  ከሰማነው፤ ለዚህ ስራ ሊተባበሩን  ቃል ከገቡ ጥቂት ባልደረቦቻችን በጣም አነስተኛ ወጪ በሚጠይቅ የመጠጥና የምግብ ግብዣ እንደዋዛ በየአካባቢያቸው የሚያዩትን ጉድና ጉዳይ ለማውራት ፈቃደኛ  ከሆኑ የፖሊስና የደህንነት አባላት ነው።

## 2. የሪፖርቱ አላማ

እኛም ይህን ሪፖርት ለእናንተ ለወገኖቻችን ስንልክላችሁ አንድ ሰሞን ጉድ ብላችሁ እንድትረሱት አይደለም። እኛ በራችንን ዘግተን ጨለማን ተገን አድርገን አልቅሰናል። እናንተም እንደ እኛ አልቅሱ። ባደባባይ ይሁን በድብቅ የማልቀሱን ምርጫ ለእናንተ ትተነዋል። ዋይ ወገኔ! ዋይ ሃገሬ! ብላችሁ ግን አምራችሁ አልቅሱ ። ለሃገራችሁ ፣ለህዝቧና በተለይ በወያኔ አሳሪዎች እጅ የወደቁት የሃገራችሁ ልጆች ስቃይ ተሰምቷችሁ እንድታለቅሱ እንፈልጋለን። አልቅሳችሁ ግን ዝም እንድትሉ አይደለም። በተለይ በውጭ ሃገር የምትገኙ ኢትዮጵያውያን በዚህ ሃገር እስር ቤቶች ውስጥ የሚፈጸመውን በዘር የተደራጀና በዘር ላይ ያነጣጠረ ጥቃት፣ በግለሰቦች ላይ የሚዘንበውን ሰቆቃ የተባበሩት መንግስታት የሰብአዊ መብት ኮሚሽን፣ የአለም የቀይ መስቀል ድርጅት፣ የሁማን ራይትስ ወች፣ የአምነስቲ ኢንተርናሺናል፣ የጄኖሳይድ ወች ድርጅት፣ በሄግ የሚገኘው የአለም አቀፍ የፍትህ ፍርድ ቤት፣ የአሜሪካን ስቴት ዲፓርትመንት፣ የአውሮፓ ፓርላማ የሰብአዊ መብት ኮሚሽን ሌሎችም በሰው ልጆች ላይ የሚፈጸሙ ግፎችን የሚዘግቡ፣ ወንጀለኞችን ለፍርድ ለማቅረብ የሚታገሉ ሁሉ እንዲያውቁት እንድታደርጉ ነው። “ምን ዋጋ አለው?” ትሉን ይሆናል። አዎን ዛሬ ምንም ዋጋ ላይኖረው ይችላል። ብዙዎቹ መንግስታትና ድርጅቶች የወያኔን ግፈኛነትና ጨካኝነት ያውቃሉ። በተለይ የምእራብ መንግስታት ይህን እያወቁ ነው አይቶ እንዳላየ የሚሆኑት። እኛን ጨምሮ በርካታዎቹን ያሰለጠኑን ለስልጠናችንም የሚሆነውን ወጪ የሸፈኑት እንግሊዞች ናቸው። በዚህም ውለታቸውና ወያኔም ኢትዮጳያዊ ለሆነ ነገር ሁሉ ባለው ጥላቻ የተነሳ የማእረግ ስማችን ሳይቀር እንደዱሮው አስር አለቃ፣ ሃምሳ አለቃ፣ የመቶ አለቃ፣ ሻምበል ወዘተ መሆኑ ቀርቶ የእንግሊዞችን የማእረግ ስሞች እንድንወርስ ተደርገናል። እኛም ሆንን ህዝባችን የማያውቀውን በቅጡ እንኳን ልንጠራው የማንችለውን፤ ለተራ ፖሊስ- ኮንስታብል፣ ለባለማእረጎቹ ምክትል ሳጅን፣ ሳጅን,፣ ሱፐር ኢንቴንዳንት፣ ምክትል ኢንስፔክተር፣ ኢንስፔክተር፣ ምክትል ኮሚሽነር ኮሚሽነር ወዘተ የሚሉ የእንግሊዝ ስሞች የተለጠፈልን እንግሊዞች መኪና፣ ዱላ፣ ልብስ እና ስልጠና ስለሰጡን ነው። ዛሬ በየእስር ቤቱ ሰው የሚገርፉት፣ በየመንገዱ ህጻናትን የሚገድሉት እነ ሃምሳ አለቃ አይደሉም ።እነ ኮንስታብል እገሌ እነ ሳጅን እገሌ፣ እነ ሱፐር ኢንቴንዳንት እገሌ ናቸው። ትእዛዝ ሰጪዎቹ እነ ምክትልና ዋና ኮሚሽነር እገሌ ናቸው። ይህንን እንግሊዞች ያውቃሉ። ይህን እያወቁ በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ ወያኔ ለሚፈጽመው ወንጀል ተባባሪ መሆንን መርጠዋል። ወያኔን በከፍተኛ ደረጃ በገንዘብ የሚደጉሙት፣ በዲፕሎማሲ

መድረኩ እክል እንዳይገጥመው ድጋፍ የሚያደርጉለት ሆነው አርፈውታል። ከዚህ በላይ የአንድ ሃገርና ህዝብ ጠላትነት ምን ሊሆን ነው? ለማለት የፈለግነው የምእራብ መንግስታት በኢትዮጵያውያን ላይ የሚፈጸመውን ግፍ አይተው እንዳላዩ እንደሚያልፉት እናውቃለን ለማለት ነው። ይህንን መረጃ ስንልክ ዛሬውኑ አንድ ነገር ይሆናል ከሚል ቅዠት አይደለም። ነገ የሚባል ነገር መኖሩን መርሳት የለብንም። የዛሬ የሃገራችን እብሪተኛ ገዢዎች ነገ ቀን ሲጎድልባቸው እነዚህን መረጃዎች አሰባስበው ከሳሽ ለመሆን የሚሽቀዳደሙት እነዚህ እንደወያኔ ይሉኝታ የማያውቁ የምእራብ ሃገሮች ስለሆኑም መረጃው በእጃቸው ቢገባ ጥቅም እንጂ ጉዳት የለውም ለማለት ነው። አቅም ያላችሁ ይህንን ዘገባ ተርጉማችሁ ለምእራብ የሚድያ ሰዎች፣ የሰው ልጅ መብት መጣስ ለሚያሳስባቸው የፓርላማ ተመራጮች የሲቪል ድርጅት መሪዎች አድርሱልን። በእናንተ በወገኖቻችን በኩል የሚደረገው ይህ ብቻ አይደለም። ይህ ብቻም በቂ አይሆንም። ይህ ዘገባ በዋነኛነት የሚያተኩረው ከግንቦት 7 ጋር በመተባበር መፈንቅለ መንግስት ልታካሂዱ ነበር ተብለው በታሰሩት በዜግነታቸው ኢትዮጵያዊ በዘራቸው በአብዛኛው አማራ በሆኑ ግለሰቦች ላይ ቢሆንም በነዚህ ግለሰቦች ላይ የደረሰው አስከፊ ሰቆቃ በሁሉም የሃገሪቱ ዜጎችና ዘሮች ላይ የሚፈጸም ነው። በግንቦት ሰባት አባልነትም ተጠርጥረው የታሰሩት በሙሉ የአማራ ዝርያ ያላቸው ብቻ እንዳልነበሩም መታወቅ ይኖርበታል። ከወያኔ ዘረኛነት የሚመጣ ጭካኔ ያላረፈበት ዘር በሃገሪቱ ውስጥ አይገኝም። የኦሮሞው፣ የጋምቤላው፣ የኡጋዴኑ፣ የሲዳማው፣ የጉጂው እና የሌላውም ዘር ስቃይና መከራ ምድሪቱ ከምትሸከመው በላይ ሆኗል። ይህን ተረድታችሁ ይህንን በሁሉም የሀገሪቱ ህዝብ ላይ የሰለጠነ የዘረኞች ጭካኔ እንዲያከትም በአንድነት ተባብራችሁ እንድትነሱ ነው። ሌላው ፍላጎታችን ዜጎች ይህን መንግስት እንደ አንድ ጤነኛ መንግስት በመውሰድ ከዚህ መንግስት ጋር እስካሁን የገቡበትን ማናቸውንም ግንኙነት በቅጡ እንዲፈትሹ ነው። በእኛ እምነት ከዚህ መንግስት ባለስልጣናት ጋር የሚወዳጁ፤ ከዚህ መንግስት ጋር ተሻርከው የሚነግዱ፤ በዚህ መንግስት ግብዣዎች ላይ የሚገኙ፤ ይህ መንግስት የሚጠይቃቸውን የሚፈጽሙ የሃገሪቱ ዜጎች ከምን አይነት ጨካኝ አረመኔ ሰዎችና መንግስት ጋር እየሰሩ እንደሆነ እንዲያውቁት ነው። የወያኔ መንግስት እጅግ አስከፊ የሆነ ግፍና ወንጀል በበርካታ የሃገሪቱ ዜጎች ላይ እየፈጸመ ነው። ከዚህ ወንጀለኛ መንግስትና ባለስልጣናት ጋር ስራችንና ኑሯችን ከሚያስገድደን በላይ መወዳጀት እራሱ ወንጀለኛ ሊያደርገን እንደሚችል ማወቅ ይኖርብናል።

## 3. ግንባር ቀደም ተጠያቂዎች

ከዚህ ቀጥሎ የሚቀርበው ዘገባ ግፉን በሚፈጽሙት የታችኛዎቹ አካላት ፍላጎትና እውቅና ብቻ የሚፈጸም አይደለም። ከጠቅላይ ሚኒስትሩ ከአቶ መለስ ዜናዊ አንስቶ ከሳቸው በታች በሆኑ ሌሎች ከፍተኛ ባለስልጣናት፣ የደህንነት ሹሞች እንዲሁም ከፍተኛ ዳኞች እያወቁት የተፈጸመና እየተፈጸመ ያለ ጉዳይ ነው። ጠቅላይ ሚኒስትሩ በቴሌቪዥንና በሬድዮ ቀርበው "በግንቦት ሰባት ስም የታሰሩት እስረኞች ድብደባ ደርሶብናል የሚሉት ሃሰት ነው" ብለው ሲናገሩ ከጹላም በላይ ያለፈ ስቃይ በቀጥታ ራሳቸው በሚሰጡት ትእዛዝ እየተፈጸመባቸው እንደሆነ ጠንቅቀው ያወቁ ነበር። ሌሎችም ባለስልጣናት አልሰማንም አላወቅንም እንዳይሉ በዚህ ሰነድ ውስጥ የተጠቀሱትን መረጃዎች በግል እንዲደርሳቸው ተደርጓል። በተለይ ወያኔን አቅፈውና ደግፈው በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ ዘረኛ የግፍ ስርአቱን እንዲዘረጋ ለረዱት የብአዴን አመራሮች እንዲደርሳቸው ተደርጓል። የሚያሳዝነው በዘገባው ውስጥ አንዳንዶቹ ታሳሪዎች በትግራይ ገራፊዎቻቸው ሲቀጠቀጡ የነበረው "የትኛው የብአዴን አመራር ነው አይዞህ ያላችሁ?" እየተባሉ፣ እነዚሁኑ ለራሳቸው ክብር የሌላቸውን አመራሮች ሳይቀር እንዲወነጅሉ ለማድረግ ጭምር እንደነበር የብአዴን አመራሮች መረጃው ደርሷቸዋል። እነዚህ የአማራንና የተቀረውንም የኢትዮጵያ ህዝብ እጅ እግሩን አስረው በወያኔ ዘረኞች ተገዶ እንዲደፈር ያደረጉ ወራዶች በጉዳዩ ላይ እስከአሁን አንድም ቃል አልተነፈሱም፤ ወደፊትም ይተነፍሳሉ የሚል እምነት የለንም። የአማራን ህዝብ እወክላለሁ የሚል ድርጅት የገዛ ድርጅቱ አባላት በሽዎች ከስራቸው ሲባረሩ፣ በመቶዎች የሚቆጠሩት እጅግ አሰቃቂ በሆነ እስር እጅግ አሰቃቂ የሆነ ቅጥቀጣ ሲፈጸምባቸው፣ የአማራ ተወላጆች በመሆናቸው ዘራቸው እየተጠራ እጅግ አሰከፊ በዘር ላይ የተመሰረተ ስድብና ውርደት ሲደርስባቸው የወያኔ ዘረኛ ገራፊዎችና ተሳዳቢዎች አጨብጫቢና አጫፋሪ መሆናቸው ወደፊት በታሪክ ፊት ውድ ዋጋ የሚያስከፍላቸው ለመሆኑ ጥርጣሬ የለንም።

## 4. ወንጀል ተብሎ ስለቀረበው ነገር

የዛሬው ሪፖርት የሚያተኩረው ወያኔ ከነጄነራል ተፈራ ማሞ ጋር ባሰራቸው ግለሰቦች ላይ በተለይ በተለምዶ ማእከላዊ ምርመራ በተባለው የምድር ሲኦል ውስጥ በደረሰባቸው እጅግ ዘግናኝ ሰቆቃ ላይ ነው። እግረ መንገዳችንን ግን ይህ እስር ቤት ምን እንደሚመስል በስር ቤቱ ውስጥ

በሌሎች ላይም ስለሚደርሰው ሰቆቃ ጥቂት ማለታችን አልቀረም። እድሜ ከሰጠን፤ እና ወያኔም በጥርጣሬ ካልደረሰብን ወደፊት እንድታውቁት የምናደርገው ብዙ የወያኔ ገበና ይኖረናል። አደገኛ ስራ ነው ትሉን ይሆናል፤ እናውቃለን። ከውርደት ህይወት ሞት ይሻላል ብለን ስለምናምን የመጣውን ለመቀበል ዝግጁ ነን። እናንተም ወገኖቻችን የእኛን ድካምና መስዋእትነት መና እንደማታስቀሩት ተስፋ አለን። የግንቦት 7 ተከሳሾችን ለመያዝ ዝግጅት የተጀመረው አብዛኛው ታሳሪዎቹ ከታሰሩበት ከሚያዚያ 16 2001 አመተ ምህረት ሁለት ቀናት በፊት ቀደም ብሎ ነበር። ለስርአቱ ያላቸው ታማኝነት በትግራይ ተወላጅነታቸው የሚለካው ጥቂቶች የምርጡ ዘር አባል የሆኑት የስራ ባልደረቦቻችን ይህ እንደሚሆን አስቀድሞ ተነግሯቸው ነበር። የትግራይ ደም የሌለን ሰራተኞች ግን የምናውቀው ነገር አልነበረም። ይሁንና ሚያዚያ 14 እና 15 ቀን 2001 አመተ ምህረት "የመረጃ ደህንነት አገልግሎትና የፌደራል ፖሊስ የጋራ የጸረ ሽብር ሃይል" በሚል የሚታወቀው በትግራይ ተወላጆች የተሞላው ቡድን በማእከላዊ ምርመራ ውስጥ በሚያደርገው ያልተቋረጠ ስብሰባ፣ አባላቱ በሚያሳዩት ያልተለመደ ጥድፊያ የተሞላበት እንቅስቃሴ፣ መንሾካሾክና ሽር ጉድ እንዲሁም ያለማቋረጥ በሚደወለው ስልክ ብዛት ይህ ቡድን እኛ የትግራይ ተወላጆች ያልሆንነው ሁለተኛ ዜጎች እንዳንሰማው የተፈለገ ትልቅ ጉዳይ እንደያዘ ለመጠርጠር አልተቸገርንም። የጠረጠርነው አልቀረም። እነዚህ ምርጥ ዘሮች በር ዘግተው ማንም የትግራይ ተወላጅ ያልሆነን ሰው ሳያማክሩ ያዘጋጁትን የአፈና እቅድ አጠናቀው ከደህንነት፣ ከፌደራልና ከመደበኛ ፖሊስ አካላት ታማኝ ናቸው ብለው የሚያስቧቸውን የራሳቸውንና ከሌላ ዘር የተቀላቀሉ ተራ ወታደሮችና ባለሌላ ማእረጎች በማሳተፍ የግንቦት 7 ተከሳሾችን መያዝ የጀመሩት ሚያዚያ 16 2001 አመተ ምህረት ከሰአት በኋላ ነበር። በዚህ የማሰር ስራ የተሰማሩት የትግራይ ተወላጅ ያልሆኑ አባላት በሙሉ የተነገራቸው ግዳጅ እንደሚወጡ እንጂ ግዳጁ ምን እንደነበር አልነበረም። ተራው የትግራይ ፖሊስ ሳይቀር ግን ግዳጁ ምን እንደነበር በደህንነቱና በፌደራል ፖሊሱ ወስጥ ወያኔ በዘረጋው የትግራይ ተወላጆች ዘረኛ መዋቅር አማካይነት ዘረኛ ከሆነ መርዝ ጋር ተቀላቅሎ እንዲያውቀው ተደርጎ ነበር። እኛንም ከሌላ ዘር የመጣን የደህንነትና የፌደራል ፖሊስ አባላትንም በአይነ ቁራኛ መጠበቅ ለወያኔዎቹ ከተሰጣቸው የስራ መደብ ጋር የተያያዘ እንደነበር አናጣውም፤ የተለመደ አሰራር ነውና።

ይህ ግዳጅ በወያኔ ዘረኛነት የተንገፈገፉ፣ በተለይ ወያኔ በአማራ ህዝብ ላይ ካለው ቂምና ጥላቻ በመነሳት የአማራን ህዝብ ቅስም ለመስበር ለማዋረድና በፖለቲካና በኢኮኖሚ ለማድቀቅና አስጎንብሶ ለመግዛት የሚፈጽመውን አስገድዶ ከመድፈር ልዩነት የሌለውን እኩይ ድርጊት በየቦታው ሲቃወሙ የነበሩ፤ የዚህ ተቃውሞ ሬኮርድ ያላቸውን የአማራ ልጆችን ከያሉበት መልቀም መሆኑን የተረዳነው ቅዳሜ ሚያዚያ 17 ቀን የመረጃ ደህንነት አገልግሎትና የፌደራል ፖሊስ የጋራ የጸረ ሽብር ሃይል በመንግስት ሚድያዎች ያሰራጩውን ዜና እኛም በግዳጁ የተሰማራነው ሳንቀር እንደማንኛውም ህዝብ በሬዲዮና በቴሌቪዝን ስናዳምጥ ነው። በእኛ እምነትና ተሰበሰበ ከተባለው መረጃ እንዳየነው ከየቦታው እየተለቀሙ የታሰሩት ሰዎች እጅግ አብዛኛዎቹ ወያኔ በሃገሪቱ ወስጥ እየገነባ የመጣውን በትግሬነት ላይ የተመሰረተ ዘረኛ ስርአት የሚቃወሙ የነበሩ ናቸው። አንዳንዶቹ እንደ ጀነራል ተፈራ ማሞ ያሉት በመቶዎች የሚቆጠሩ ሰዎች ባሉባቸው የብአዴን ስብሰባዎች ላይ ይህን አስተያየት በአደባባይ ሲሰጡ የተቀዱት ቪድዮ በማእከላዊ ምርመራ ጽ/ቤት ይገኛል። አንዳንዳዶቹ ታሳሪዎቹም ራሳቸው በፍርድ ቤት ቀርበው በሰጡት ቃላቸው በአማራ ህዝብ ላይ የሚደርሰውን በደል በሃገሪቱና በህዝቡ ህይወት ውስጥ ወያኔዎች ዘረኛ በሆነ መንገድ እየገነቡት ስላለው ፍጹማዊ ዘረኛ የበላይነት ለራሱ ለብአዴን አመራር ሳይቀር እንደነገሩና እንዳስጠነቀቁ ተናግረዋል። ይህን በፍርድ ቤቱ ውስጥ ተከሳሾቹ ራሳቸው ለችሎቱ ሲናገሩ በጆሮአችን ከሰማን በኋላ ሰዎቹ በተለይ የጦር መኮንኖቹ እንዲታሰሩ ግፊቱን ሲያደርጉ ከነበሩት መሃል ዋንኛዎቹ ራሳቸው ስጋቸውን ብቻ ሳይሆን ነፍሳቸውን ለወያኔ የሸጡ የብአዴን አመራሮች ናቸው የሚል ወሬ በማእከላዊ ምርመራ በስፋት ተወርቷል። ከግንቦት 7 ጋር ግንኙነት ነበራቸው የሚለውን ክስ ለማመን የተቸገርነውም ለዚህ ነው። ግንቦት 7 ህብረ_ብሄራዊ ድርጅት ሆኖ ሳለ በግንቦት 7 ነት ተከሰው የተያዙት ሰዎች በሙሉ ከዶክተር ብርሃኑ ዘመድ በስተቀር አማሮች ሆነው መገኘታቸው ግንቦት 7ን ሽብርተኛ ብሎ ለማወጅ ከመፈለግ ሌላ ከታሳሪዎቹ ጋር የሚያገናኘው ነገር ያለ አልመሰለንም። ወያኔ በራሱ በብአዴን ሰዎችና በራሱ የስለላ ድርጅት የወያኔን ዘረኛ የበላይነት ይቃወማሉ፤ የአማራ ህዝብንና ምሁራንን እንዲሁም በሰራዊቱ በፌደራልና በመደበኛ ፖሊሱ ውስጥ የሚገኙትን አማሮችን ይቀሰቅሳሉ የሚላቸውን ሰዎች ለይቶ እንዳሰረ ነው የምንረዳው። የታሰሩት ሰዎች ማንነት የሚያሳየውም ይኸንኑ ነው። ይህን የመሰለ ስራ መስራት ወያኔ የለመደበት ነው። ኦነግን ሰበብ እያደረገ በወያኔ ላይ ተቃውሞ ያላቸውን በአስር ሺዎች የሚቆጠሩ የኦሮሞ ምሁራን፣

የሰራዊትና የፖሊስ አባላት እያፈኑ በየእስርቤቱ እያጎረ ለከፍተኛ ስቃይ የዳረገበት ዘዴ ነው። ወያኔ በአደባባይ ወጥቶ "እነዚህን ኦሮሞዎች ወይም አማሮች የገደልኩት ያሰርኩት ዘረኛ የበላይነቴን ስለተቃወሙ ነው" እንዲል የሚጠብቅ ካለ፣ እሱ የዋህ ነው። ሽብር ለማካሄድ ህገ መንግስት ለመናድ ቫትና ግብር ባለመክፈል ወዘተ የሚሉ ሰበቦች ያስፈልጉታል። ግንቦት ሰባት፣ ኦነግ፣ ኦብነግ የሚባሉ ድርጅቶች ስም በየክሱ የሚነሳውም በዘር ላይ የተመሰረተ ጥቃት ለመሸፈን ነው። ሚያዝያ 16 ቀን 2001 አመተ ምህረት መጀመሪያ በመፈንቅለ መንግስት በማግስቱ ደግሞ ክሱ ተቀይሮ በሽብርተኛነት የተከሰሱት ሰዎች አፈና የተካሄደው በሁሉም የሀገሪቱ ክልል ነበር። ከጎንደር እስከ ሃረር ድረስ በሚገኘው የሃገሪቱ ክልል የወያኔን ዘረኛነት የሚቃወሙ በርካታ ግለሰቦች እንደ አውሬ እየታደኑ ተይዘዋል። በይፋ ለፍርድ ቤት የቀረቡት ከሃምሳ የማይበልጡ ግለሰቦች ቢሆኑም የወያኔ የደህንነት አባላት በሚቆጣጠሯቸው የየክልሉ የምርመራ ጣቢያዎች የታሰሩትና እጅግ አሰቃቂ ሰቆቃ የተፈጸመባቸው የሰራዊቱ ፣ የፌደራል ፖሊስ፣ የመደበኛ ፖሊስ አባላትና የሲቪሎች ቁጥር ከመቶዎች አልፎ ወደ ሽዎች እንደሚጠጋ መረጃዎች ይጠቁማሉ። በተለያዩ የሙያ ዘርፎች በተሰማሩ ወጣት ምሁራን በጎልማሶች፣ በአረጋውያን፣ በሴቶችና በወንዶች ላይ አመቃው ተካሂዷል። ለፕሮፓጋንዳ ፍጆታ ሆን ተብሎ ከተቀነባበረው የጥቂቶች አያያዝ በስተቀር ብዙዎቹ እስረኞች ያለምንም የፍርድ ቤት ትእዛዝ የተያዙና ያለምንም የፍርድ ቤት ትእዛዝ ቤታቸው የተበረበረባቸው ንብረታቸው የተዘረፈባቸው ነበሩ። የወያኔን መንግስት በአመጽ ለመገልበጥ አሲረዋል ከተባሉት መሃል አንዳንዶቹ ስርአቱን ከሚያገለግሉበት ቦታ የተያዙ ናቸው። አንዳንዶቹ ማእከላዊ እንድትመጣ ትፈለጋለህ ተብለው በራሳቸው ሄደው የተያዙ ናቸው። አንዳንዶቹ አማን ብለው ከተቀመጡበት ቤታቸው የተወሰዱ ሲሆኑ፣ ከንግድ ድርጅቶቻቸው ላይም እጅግ አስደንጋጭና አሸባሪ በሆነ ሁኔታ መትረየስና ክላሽን ያነገቡ በሃያዎችና በሰላሳዎች የሚቆጠሩ የደህንነትና የፌደራል ፖሊስ አባላት ከበውና አዋክበው የያዟቸውም አሉ። ከእነዚህ እስረኞች ውጭ በወያኔ የደህንነት አባላት እየታፈኑ ከተለያዩ መስሪያ ቤቶችና የግል መኖሪያቸው የተወሰዱ እስካሁንም የት እንደደረሱ የማይታወቁ በብዙ መቶዎች የሚቆጠሩ የአማራ ተወላጆች አሉ። በጥርጣሬ ብቻ ከመከላከያ፣ ከፖሊስና ከፌደራል ፖሊስ ስራቸውና መንግስት ከሰጣቸው የኪራይ ቤቶች ተባረው ቤተሰባቸውና ራሳቸውም ለረሃብና ለእንግልት የተዳረጉ በብዙ ሺዎች የሚቆጠሩ ዜጎችም እንዳሉ መረሳት የለበትም።

## 5. ማእከላዊ ምርመራ

በማእከላዊ ምርመራ ስለደረሰው ሰቆቃ የያንዳንዳቸውን ስም እየጠራን ከማቅረባችን በፊት “ማእከላዊ ምርመራ” ስለሚባለው ተቋም ትንሽ ማለት ያስፈልጋል። ማእከላዊ ምርመራ በተለያዩ ተከታታይ መንግስታት ዘመን፣ መንግስት በወንጀል የሚከሳቸው ሰዎች፣ በተለይ መንግስት ጉዳያቸውን ሊያጠብቅባቸው የሚፈልጋቸውን ታሳሪዎች በጥብቅ እስርና ምርመራ እንዲሰቃዩ የሚያደርግበት ቦታ ነው። ይህ ቦታ እንደ ደርግ ግዜ ባይሆንም በንጉሱ በአጼ ሃይለስላሴም ዘመን ጥብቅ ምርመራ የሚካሄድበት፤ አልፎ አልፎ መርማሪዎች ከታሳሪዎች ማግኘት የሚፈልጉትን ማስረጃ ለማሰባሰብ የተለያዩ የአካልና የመንፈስ ሰቆቃ የሚፈጽሙበት ቦታ ነበር። በንጉሱ ግዜ ማእከላዊ ምርመራ በደርግ ግዜ የተፈጸመውን አይነት ግፍና ስቃይ በእስረኛ ላይ የሚፈጸምበት ቦታ አልነበረም። ለራሳቸው ክብር የነበራቸው የንጉሱ ዘመን ዳኞች እስረኛን በማሰቃየት የተገኘን መረጃ ውድቅ የሚያደርጉ ስለነበሩ መርማሪዎች ሰው አሰቃይተው በሚያገኙት መረጃ የሚያገኙት ጥቅም ስላልነበረ ግርፋትና ዱላ ዋንኛው የመመርመሪያው ዘዴ አልነበረም። ማእከላዊ ምርመራ በስቃይ ቦታነት ዝናው የገነነው በደርግ ዘመን ነው። በማእከላዊ ምርመራ ውስጥ በደርግ ዘመን በሃገሪቱ ዜጎች ላይ በተለይ በምሁራኑና በወጣት ተማሪዎች ላይ የተፈጸመውን ግፍ እዚህ መዘርዘሩ አያስፈልግም። እጅግ ዘግናኝና አሰቃቂ ነበር። የአጼ ሃይለስላሴ መንግስት ወድቆ የደርግ መንግስት ስልጣን ሲይዝ የማእከላዊ ምርመራ መርማሪዎች ወደ አዲሱ መንግስት መርማሪነት ተሸጋገሩ። እነዚህ እዛው የቀሩት መርማሪዎች የደርጉን ስርአት የመርማሪነት መስፈርት በማሟላት ደርግ የሚፈልገውን በማሰቃየትና በሰቆቃ ላይ የተመሰረተ ምርምራ ለማካሄድ ፈቃደኛ የነበሩ ናቸው። ለእንዲህ አይነቱ አሰራር ህሊናቸውን ማስገዛት ያልቻሉት ስራቸውን በፈቃዳቸው ለቀቁ። ደርግ ወድቆ ወያኔ ስልጣን ሲይዝ ለፕሮፓጋንዳ ፍጆታ ሲባል በማእከላዊ ምርመራ ህዝብ በመግረፍና በማሰቃየት የታወቁት ጥቂት ግለሰቦች በአደባባይ ስማቸው ተጠርቶ ወህኒ ቢወርዱም ደርግ እንዳደረገው ሁሉ ወያኔም ቀድሞ ከነበረው ስርአት የወረሳቸው መርማሪዎች አሉት። ጥቂቶቹ ዛሬ ወያኔ በማእከላዊ ምርመራ ለሚፈጽመው ሰቆቃ “በባለሙያነት” እያገለገሉ ናቸው። የአሁኑን የማእከላዊ ምርመራ በተከታታይ መጥተው ካለፉት መንግስታትና ዘመናት የሚለየው የምርመራ ተቋሙን በከፍተኛ ደረጃ የሚመሩት ግለሰቦች በሙሉ ከአንድ የትግራይ ዘር የተውጣጡ መሆናቸው ዋንኛው ነው።

ተቋሙ ዘረኛ በሆነ መንገድ ለመጀመሪያ ግዜ የተደራጀው በዘመነ ወያኔ መሆኑ ነው።

ይህን ዘገባ ባጠናቀርንበት ወቅት በዚህ የማሰቃያ ማእከል በብዙ መቶዎች የሚቆጠሩ እስረኞች በዚህ ምድር ላይ ይሆናል ተብሎ የማይጠበቅ ሰቆቃ እየተፈጸመባቸው ነበር። በዚህ የማሰቃያ ቦታ የኦሮሞና የኦጋዴን ነጻ አውጭ ድርጅቶች አባላት ናችሁ ተብለው እጅግ አሰቃቂ ግፍ የተፈጸመባቸው እስረኞች ይገኛሉ።

አንድ አቶ ሃሰን የሚባል ከደጋሃቡር ታፍኖ የመጣ የኦጋዴን ዝርያ ያለው እስረኛ ፍርድ ቤት ሳይቀርብ ከሁለት አመት በላይ ታስሮ ይገኛል። ጭራሹኑ ፍርድ ቤት ቀርቦ አያውቅም። ስድስት ወራት ሙሉ እጁ በካቴና፤ እግሩ በእግር ብረት ታስሮ ነው የቆየው። በድብደባ ብዛት የግራ ዘር ፍሬው /ብልቱ/ አንዱ ሚሙቶ ጠፍቷል። እንደ ከብት የወንድን ልጅ ብልት በመቀጥቀጥ ዘር አልባ ማድረግ በዛ ክፉ በሚባለው የደርግ ግዜ እንኳን ያልነበረ ነበር። በወያኔ ዘመን ግን ይህ የማሰቃያ ዘዴ በስፋት እየተሰራበት ነው። ከምርጫ 97 በኋላ በተለይ በአማራ ክልል ውስጥ የቅንጅት ጠንካራ ደጋፊ የነበሩ ገበሬዎችን የወያኔ ካድሬዎች ሱሪያቸውን እያስወለቁ ብልታቸውን ይቀጥቅጧቸው ነበር የሚል ዜና ሲሰማ ብዙዎች ለማመን ይቸገሩ ነበር። በወያኔ እስር ቤቶች የሚካሄደውን ጉድ በአይኑ መመልከት፤ በጆሮው መስማት የዘወትር ውሎው ለሆነው እኛን ለመሰለውና በስር ቤቶች አካባቢ ለሚሰራው ሌላውም ሰው ግን አስገራሚ አይደለም። ሁላችንም እዚህ ማእከላዊ እስር ቤት በበርካታ የሃገሪቱ ዜጎች ላይ ሲፈጸም እያየነው ነው። የጥቃቱ ሰለባ የሆኑ ዜጎችን እና ቤተሰቦቻቸውን ቤታቸው ይቁጠሯቸው:: ይህ ሃሰን የተባለ የኦጋዴን ሰው በኤሌክትሪክ መላ ሰውነቱ ተጠብሷል። አንዳንዴም ሁኔታውን ላጤነው ይህ ሰው በሳይንስ ላብራቶሪ ሰንዱቅ ውስጥ ተቀልፎባቸው አዲስ መድሃኒት እንደሚሞከርባቸው አይጦች ቆጥረውት ይሆን ወይ ያሰኘናል።

የዘረኛዎቹ የወያኔ ባለስልጣናት እንደ አይጥ ቆጥረው የማሰቃያ ጥበብን የሚመራመሩት በአቶ ሃሰን ብቻ አይደለም። ከነቀምት፣ ከአምቦ፣ ከምስራቅ ሀረርጌ እና ከከሚሴ ታፍነው መጥተው ማእከላዊ ምርመራ ጣቢያ ከ6 ወራት በላይ ከፍተኛ ስቃይ ስለደረሰባቸው ወገኖቻችን ስናስብ ሃዘናችን ይበረታል። እነዚህ 12 የኦሮሞ ዝርያ ያላቸው ወጣቶች ናቸው። እጃቸው በካቴና ታስሮ በግድግዳ ላይ ይሰቀላሉ፣ ይዘቀዘቃሉ፣

በኤሌክትሪክ ይገረፋሉ። ከነዚህ መሃል ሶስቱ ብልታቸው ላይ በደረሰባቸው ግርፋት ምክንያት ሽንታቸውን መቆጣጠር አይችሉም። አንዳንዶቹ ብልታቸው ላይ በደረሰባቸው ግርፋት የተነሳ ተኮላሽተዋል። አንዳንዶቹ አካላቸው ጎድሏል፤ አይናቸው ጠፍቷል፤ እጃቸው ተሰብሯል፤ ጥፍራቸው ተነቅሏል። ከአስራ ሁለቱ መሃል ሁለቱ በሰርጋቸው እለት ነው የታፈኑት። ከእነዚህም ሌላ እጃቸውንና እግራቸውን በካቴና ታስረው ቀንም ለሊትም በጨለማ ቤት ውስጥ ተዘግቶባቸው እዛው እስር ቤት ውስጥ የሚኖሩት ሁለት እድሚያቸው ከ15 አመት በታች የሆኑ ወጣት ልጆች አሉ።

በ1987 አመተ ምህረት በግብጹ መሪ ግድያ ሙከራ ላይ ተሳትፈዋል ከተባሉት ሶስቱ አንዱ እዛው በህመም ሲሞት ሁለቱ ከ15 አመት በላይ ፍርድ ቤት ሳይቀርቡ ማእከላዊ ታስረው ቆይተዋል። እንግዲህ የግንቦት ሰባት ተከሳሾች እየተባሉ የሚጠሩት እስረኞች ከተለያዩ የሃገሪቱ ከተሞችና ክልሎች ተሰባስበው የታጎሩት እንዲህ አይነቱ ግፍና ሰቆቃ በሚፈጸምበት፣ የትግራይ ተወላጅ በሆኑ የወያኔ አባላት ፍጹም ዘረኛ ቁጥጥር ስር ባለ የምርመራ ጣቢያ ውስጥ ነው። እጣቸው ምን ይሆናል ለሚለው ጥያቄያችሁ ከእስረኞቹ መሃል የጥቂቶቹን ምርመራ በሚመለከት ያጠናቀርነው ዘገባ እነሆ ። በቅድሚያ ግን ላለመደጋገም በሁሉም ላይ በጋራ የተፈጸመውን እናስቀድም።

## 6. በግንቦት 7 ተከሳሾች ላይ ስለተፈጸሙ ሰቆቃዎች

### ሀ) በሁሉም የግንቦት ሰባት ተከሳሾች ላይ የተፈጸሙ ሰቆቃዎች

*ቀደም ብለን እንደገለጽነው በርካታ ታሳሪዎች እጃቸው የተያዘው ሚያዝያ 16 2001 ነው። የታሳሪዎቹ ብዛት በመጨረሻ ተከሰው ፍርድ ቤት በአካል ከቀረቡት 37 ሰዎች እጅግ የላቀ ነው። እንደ ኮሎኔል የሺዋስ አይነቱ በድለላና በፍቃደኛነት፤ ገበያው አይችሉህም አይነቶቹ በድብደባ ብዛት በጓደኞቻቸው ላይ መስካሪ ሆነው ለመቅረብ ፈቃደኛ በመሆናቸው ሚያዝያ 16 2001 ከታሰሩት መሃል የተለቀቁም አሉ። ሚያዝያ 16 2001 ከተያዙት በተጨማሪ ለወያኔ መስካሪ ለመሆን በተስማሙት ሰዎች ጥቆማ የተያዙ እየተባለ ወያኔ በተለይ በሰራዊቱ ውስጥ ራሱ የሚጠረጥራቸውን የአማራ መኮንኖች እና ፖሊሶች እስከ ግንቦት 2001 የመጀመሪያ ሳምንት ድረስ ሲያስር ነበር። ለምሳሌ ከሃረር ተይዘው የመጡት*

ወታደራዊ መኮንኖች 13ኛ ተከሳሽ ሻለቃ መሰከረ ካሳ፣ 6ኛ ተከሳሽ ሌ/ኮ አበረ 7ኛ ተከሳሽ ሌ/ኮ አለሙ ጌትነት የተያዙት ሚያዚያ 21 ቀን ነው። ጥቂት ሰዎች ግንቦት ወር መጀመሪያ ገደማ ታስረዋል። ሁሉም ታሳሪዎች ማእከላዊ ምርመራ ግቢ ሲደርሱ እጃቸው በካቴና ታስሮ አይናቸው በጨርቅ ተሸፍኖ እየተጎተቱ ነው ወደ ተዘጋጁላቸው የእስር ክፍሎች የተወሰዱት። የተወሰኑት በጋራ በአንድ ክፍል ውስጥ የታሰሩ ሲሆን ወያኔ በከፍተኛ ጥላቻ የሚመለከታቸው ግን ተለይተው ለብቻቸው በጠባብ ክፍል ውስጥ ታስረው እንዲቆዩ ተደርጓል። የእስረኞችን የምግብና የመኝታ ሁኔታ እዚህ ማንሳቱ በሚቀጥሉት ቀናት ከተፈጸሙባቸው ግፍ ጋር ሲወዳደር ቅንጦት ስለሚመስል ማለፉን መርጠናል። እህል ውሃ እንዳይቀምሱ ተደርገው ለቀናት የታሰሩ እንደበረዶ በሚቀዘቅዝ የሲሚንቶ ወለል ላይ በለበሱት የቀን ልብስ ውለው እንዲያድሩ የተደረጉ እስረኞች ነበሩ። እስረኞቹ በሙሉ በተያዙ በጥቂት ቀናት ውስጥ እጃቸው በካቴና እየታሰረ አይናቸው በጨርቅ እየተሸፈነ ማንንም ማየት በማይችሉበትና ማንም እንዳያያቸው በሸራ በተሸፈነ መኪና ለማእከላዊ ምርመራ ቅርበት ባለው የአራዳ ጊዮርጊስ አንደኛ ችሎት ፍርድ ቤት እየቀረቡ ፖሊስ የምርመራ ስራውን እስኪጨርስ በሚል በእስር እንዲቆዩ እየተወሰነባቸው ወደ ማእከላዊ ምርመራ ተመልሰዋል። በእነዚህ እስረኞች ላይ የተካሄደው ትልቁና ዋናው አሰቃቂ ሰቆቃ የተፈጸመው ፍርድ ቤቱ ለፖሊስ በሰጠው የምርመራ ጊዜ ውስጥ ነው። እነዚህ ተከሳሾች እስር ቤት ከታጎሩበት ቀን ጀምሮ የሚደርስባቸውን ግፍ እና የምርመራ ሂደት ጋር በቅርበት የምናውቀው ሰዎች እንደተረዳነው የጸረ- ሽብር መስሪያ ቤቱ ሊፈጽም ነበር ብሎ ላቀረበው መንግስት የመገልበጥ ከፍተኛ የሽብር ሙከራ አንድን ነጻ ፍርድ ቤት ሊያሳምን የሚችል ምንም አይነት መረጃ በጁ ያልነበረው መሆኑን ነው። በቴሌቪዥን የቀረቡት ሰባራ ክላሽኖች ከመሳሪያ ነጋዴዎች እጅ የተያዙ እዛው ማእከላዊ ምርመራ ለረጅም ግዜ በኤግዚቢትነት ተቀምጠው የነበሩ ሲሆን የተቀሩትም ከወታደራዊ መኮንኖቹ በተለይ ለጀነራል ተፈራ ማሞ መንግስት እራሱ ለራሳቸው ጥበቃ የሰጣቸው ክላሽኖችና ሽጉጦች ሲሆኑ ከዛም ውጭ የቀረቡት መሳሪያዎች እራሱ ወያኔ ለሲቪል ታሳሪዎች ከ16 አመት በፊት ማመልከቻ አስገብተው ፈቃድ የሰጠባቸው ነበሩ። ከነዚህ መሃል ማእከላዊ ምርመራ ለወንጀል ማስፈጸሚያ የተከማቹ በማለት ያቀረባቸው ከ83 አመቱ ከአቶ ጽጌ ሃብተማሪያም ተገኙ

ያላቸው አንድ ኮልት 38ና አንድ ታጣፊ ክላሽን አዛውንቱ ከአንድ አቶ ገብረ መድህን ከሚባል የትግራይ ተወላጅ ላይ የደርግ መንግስት ሊወድቅ አካባቢ በ4800 ብር ገዝተው ለራስና ንብረት መጠበቂያነት በራሱ በመንግስት ፈቃድ ተሰጥቷቸው የያዙት ለመሆኑ ከነፈቃዱ ማእከላዊ ምርመራ እንደተመዘገበ ነው የመፈንቅለ መንግስት መሳሪያ ተብሎ በቴሌቪዢን የቀረበው። በሌላም መልኩ አንዱ እስረኛ ከሌላው ጋር ሲነጋገር እንደነበርና ምን እንደተባባለ የሚያስረዳ በድምጽ የተቀረጸ መረጃ ማቅረብ አልተቻለም። ታሳሪዎቹ አንዳቸው ላንዳቸው፣ ጀነራል ተፈራ 50 ግዜ ለጀነራል አሳምነው፣ ጀነራል አሳምነው 15 ግዜ ለኮሎኔል ደምሰው ደውለዋል፤ የሚል የስልክ ቁጥርና የደወል ብዛት ካልሆነ በስተቀር ሰዎቹ ደውለው ይህን ተነጋገሩ የሚል በድምጽ የተቀረጸ መረጃ ማእከላዊ ምርመራ ሊያቀርብ አልቻለም። በቴሌቪዢን የቀረበው የውጭ ገንዘብ ምንዛሪ ከግንቦት ሰባት ጋር ግንኙነት አላችሁ ተብለው ከታሰሩ በኋላም ፍርድ ቤቱ በነጻ ከለቀቃቸው አቶ ጌቱ ወልዴ የተባሉ ነጋዴ ታሳሪ እጅ የተያዘ ነበር። አቶ ጌቱ በወቅቱ ገንዘቡ ከየትና እንዴት በጃቸው ሊገባ እንደቻለ በቂ ምላሽ የሰጡበት ጉዳይ ነበር። ከዚህ ውጭ በማስረጃነት የቀረቡት የመገናኛ መሳሪያዎች ለወንጀል መፈጸሚያነት ለመዘጋጀታቸው መርማሪዎቹ እንኳን አንድን ነጻ ፍርድ ቤት ቀርቶ በወያኔ ካድሬዎች የተሞላን ፍርድ ቤት ማሳመን የሚችሉ አልነበሩም። ሁለት የሳተላይት ቴሌፎኖችና አንድ የሳተላይት ኢንተርኔት መገናኛ ከሰዎች እጅ አገኘሁ ብሎ መፈንቅለ መንግስትን ለሚያክል ትልቅ ነገር ተዘጋጅተው የነበሩ የመገናኛ መሳሪያዎች በማለት እነዚህን መሳሪያዎች ማቅረብ የሚያስቅ ነው። በዚህ ላይም የስርአቱን የውሸት መረጃ የማቅረብ ልምድ ለምናውቀው ሰዎች፣ እውን እነዚህም የተባሉት እቃዎች በታሳሪዎቹ እጅ ነበሩ ወይስ ወያኔ እንደለመደው ራሱ በታማኞቹ አማካይነት በየታሳሪዎቹ ቤት እያስቀመጠ አገኘሁት አለ የሚል ጥያቄ የሚያስነሳ ነው። ማእከላዊ ምርመራ በመረጃነት ያቀረባቸው ሰነዶችም ማንም ሰው በቀላሉ ሊያገኛቸው የሚችል በአብዛኛው የኢንተርኔት ተጠቃሚ ዜጋ፣ በራሳቸው በመርማሪዎቹና በአለቆቻቸው ቤት የሚገኙ ጽሁፎች ናቸው። ግንቦት ሰባት ያወጣውን ጋዜጣዊ መግለጫ፤ የዶክተር ብርሃኑን ንግግሮች፤ የግንቦት7 ን ድርጅታዊ መርሃ ግብር፤ በተለያዩ ጉዳዮች ላይ በኢትዮጵያ ድረገጾች ላይ የወጡ መንግስትን የሚቃወሙ ጸሁፎች

በግለሰቦች ቤት መገኘታቸው ለመፈንቅለ መንግስት መዘጋጀታቸውን ያሳያል በሚል በመረጃነት ቀርቧል። ይሁንና መርማሪዎቹ ሌላው ሁሉ ቀርቶ የፈለጉትን ለማስፈጸም በሚችሉበት በወያኔ ካድሬዎች በተሞላ ፍርድ ቤት እነዚህን መረጃዎች ይዞ መሄድ ያስፈራቸው በመሆኑ እስረኞቹን ወንጀለኛ ለማድረግ ጉዋደኞቻቸው እንዲመሰክሩባቸው ወይም ራሳቸው ታሳሪዎቹ የራሳቸውን ወንጀለኛነት እንዲያምኑ ማድረግ ነበረባቸው። የታሳሪዎቹ ስቃይ የሚጀምረው መርማሪዎቹ የሚፈልጉትን በሙሉ በሰው ምስክርነት ወይም በታሳሪዎቹ የእምነት ቃል ለማስደገፍ በሰሩት የግፍ ስራ ነው።

በቅድሚያ መርማሪዎቹ በቀላሉ ሊሰበሩና የምንፈልገውን ይሰጡናል ያሉዋቸውን ታሳሪዎች በመለየት በድለላና በዱላ በተቀሩት እስረኞች ላይ ምስክርነት የሚሰጡ ሰዎች አሰባሰቡ። ከዛ በኋላ ፊታቸውን ያዞሩት በተቀሩት እስረኞች ላይ ነበር። እያንዳንዱ እስረኛ ከምሽቱ 2 ሰአት ጀምሮ እስከ ውድቅት ድረስ ባለው ግዜ ከታሰረበት ክፍል እጁ በካቴና አይኑን በጨርቅ እየታሰረ ተወስዶ ፊታቸውን በማያያቸው መርማሪዎች ፊት የሰራው ወንጀል ምን እንደሆነ፣ ለተሰራው ወንጀል መርማሪዎቹ በቂ ማስረጃ እንዳሰባሰቡ ስለዚህም ሌላ መከራ ውስጥ ከመግባቱ በፊት ጥፋተኛነቱን አምኖ የእምነት ቃሉን እንዲሰጥ ይገደድ ነበር። በመጨረሻ ለፍርድ ከቀረቡት ታሳሪዎቹ መሃል የመርማሪዎቹን ምክር አዘል ማስፈራሪያና ዛቻ ሰምቶ ጥፋተኛ ነኝ ያለ አንድም እስረኛ አልተገኘም። ይህ የማስፈራራትና የማግባባት ስራ የትም እንደማያደርስ የተረዱት መርማሪዎች ወደ ሌላው የማሳመኛ ምእራፍ የተሸጋገሩት ከዚህ በኋላ ነው። አብዛኞቹ እስረኞች በማእከላዊ ምርመራ ያሳለፏቸው 45 የስቃይ ቀናት ግርፋቱ፣ ስቅላቱ፣ የአካልና የመንፈስ ሰቆቃው ተጀመረ። ለአብነት ያህል በተወሰኑት ታሳሪዎች ላይ የደረሰውን ግፍ ከዚህ በታች ለመዘርዘር ሞክረናል።

## ለ) 16ኛ ተከሳሽ መቶ አለቃ አባቡ ተፈሪ

መቶ አለቃ አባቡ ተፈሪ የተያዘው ባህር ዳር ከተማ ከሌሎች 16 ሰዎች ጋር ነው። በዚህ ሰው ላይና አብረውት ወደ ማእከላዊ በተላኩት ተጨማሪ 10 እስረኞች ላይ ቅጥቀጣ የተጀመረው ማእከላዊ

መምሪያ ከመድረሳቸው በፊት እዛው ባህር ዳር ውስጥ መ.ኮ.ድ ተብሎ በሚጠራው ወታደራዊ ካምፕ ውስጥ ነበር። እስረኞቹ ከባህር ዳር መ.ኮ.ድ ወታደራዊ ካምፕ በካቴና ታስረው ግንቦት 10 ቀን 2001 አመተ ምህረት ማእከላዊ ምርመራ ሲገቡ ፊታቸው የቆሰለ፣ ያበጠ አይናቸው ደም የሚያነባ፣ መራመድ አቅቶአቸው የሚያነክሱ ነበሩ። መቶ አለቃ አባቡ ማእከላዊ በደረሰ በማግስቱ ምሽት ላይ ነው በማእከላዊ ምርመራ መርማሪዎች እየተደበደበ ወንጀሉን እንዲያምን ጥያቄ ይቀርብለት የነበረው። እጁን በካቴና እየታሰረ አይኑን ተሸፍኖ በብረት ማንጠልጠያ ላይ በወፌ ላላ እስር ታስሮ ውስጥ እግሩን ተገርፏል። ልብሱን በሙሉ አውልቆ መሬት ላይ እንዲተኛ እየተደረገ የስቃይ ጩኸቱ ለገራፊዎቹና ለሌላም ሰው ጆሮ እንዳይደርስ አፉ በገማ ጨርቅ እየተጠቀጠቀ ጭንቅላቱን እጆቹን ጣቶቹን ታፋውን ሽንጡን በዱላ ሲቀጠቀጥ በኤሌትሪክ ገመድ እየተገረፈና በእርግጫ እየተመታ ለቀናት ተሰቃይቷል። ይህ እስረኛ እንደሌሎቹ እስረኞች አይኑን እንደተሸፈነ መርማሪዎቹ ወንበር ላይ አስቀምጠው እየተገባበዙ ባሳረፉበት ጥፊ ብዛት ጆሮው ለረጅም ግዜ ታሞ የነበረ ሲሆን አሁንም አንድ ጆሮው ታማሚ ሆኖ ቀርቶአል። መቶ አለቃ አባቡ ተፈሪ በማእከላዊ መርማሪዎች እጅ ስቃዩን በሚያይበት ወቅት በተለይ መርማሪዎቹ መሃል አማራ የሆነ ሰው በሌለባቸው ወቅቶች የትግራይ ተወላጆች መርማሪዎች ዘረኛ የስድብ ጎርፍ ይወርድበት ነበር። ዘሩን በመጥቀስ “ግም አማራ”፤ “ብስብስ አማራ”፣ “አማራ ሽንታም መሆኑን አታውቅም እንዴ?” “እዚህ አንተን ብንጠብስህ ሽታው ለአማራ ህዝብ የሚደርሰው ይመስልሃል?”፤ “በኛ እጅ የገባና ኤድስ የያዘው አንድ ነው”፤ “በኤድስ ቫይረስ የተሞላ ደም እንድንወጋህ ትፈልጋለህ?” “አንተን እዚህ ልንደፋህ እንችላለን፣ የፈለግንበት ወስደን እሬሳህን መጣል እንችላለን የሚጠይቀን የለም” የሚሉ ስብእናውን የሚነኩ አእምሮውን የሚያውኩ የስነ ልቦና ሰቆቃ ጭምር ተፈጽሞበታል። ይህ እስረኛ ለረጅም ቀናት ያለማቋረጥ በተካሄደበት ስቃይ የተነሳ በመጨረሻ መርማሪዎቹ የፈለጉትን በሙሉ ፈርሞላቸውል። ለዚህ ድል የበቁት መርማሪዎች ሰውየውን መስበር በመቻላቸው ሲመሰጋገኑ ሲፈነድቁ ማእከላዊ ምርመራ አልበቃ ብሏቸው እንደነበር ይታወቃል።

ሐ) 30ኛ ተከሳሽ ም/ሳጅን ጎበና በላይ

በዚህ እስረኛ ላይም ከላይ በአስረኛው ተከሳሽ ላይ የደረሰው የአካልና የመንፈስ ሰቆቃ ደርሶበታል። በሌሊት እየተወሰደ እንደእባብ ይቀጠቀጥ ነበር። በኤሌክትሪክ ገመድ ተገርፏል በኤሌትሪክ ሃይል ተቃጥሏል። ተሰቅሎና ተዘቅዝቆ ተገርፏል። ልብሱን በሙሉ የውስጥ ሱሪውን ሳይቀር እንዲያወልቅ ተደርጎ መርማሪዎቹ እየተፈራረቁ ቆዳው እስኪላጥ ገርፈውታል። የጋይንት ሰው መሆኑን መሳለቂያ በማድረግ "ከሃምሳ ጋይንት አንድ አጋንንት ይሻላል፣ አንተ ሆዳም ጋይንቴ" የሚሉ ስድቦችን እያወረዱ ሌሎችንም አጸያፊ ክብርና ስብእና ነክ ስድቦች እየተሳደቡ ያዋርዱት እንደነበር ለማወቅ ችለናል። ይህ ሁሉ ሰቆቃ የተፈጸመው መርማሪዎቹ የሚፈልጉትን ሁሉ እንዲያምንላቸው ነው። ለመወንጀል የሚፈልጓቸውን ሰዎች እንዲወነጅልላቸው ነበር። ሳጅን ኀበና ለበርካታ ምሽቶች ያለማቋረጥ በደረሰበት ግርፋትና ስቃይ በመጨረሻ ተሸነፈ። መርማሪዎቹ ጽፈው ያቀረቡለትን ቃሌ ነው ብሎ ፈረመ። ይህ መረጃ ነው በፍርድ ቤት ራሱንም ሆነ ሌሎችንም ባልደረቦቹን ለእድሜ ልክ እስራት የዳረጋቸው። በሳጅን ኀበና እና በሌሎችም እስረኞች ላይ ምርመራ እንዲያደርጉ ከተመደቡ በርካታ መርማሪዎች መሃል እስረኞቹን በተለያየ ደረጃ ሲያሰቃዩ የነበሩት 10 መርማሪዎች ናቸው። ከነዚህ 10 መርማሪዎች መሃል የተለየ ጭካኔ በመፈጸም የሚታወቁ አሉ። ከነዚህ መርማሪዎች ጋር እየተመሳጠረ በተመርማሪዎቹ ላይ የተፈጸመውን አሰቃቂ የዱላ ውርጅብኝ ከሰውነታቸው ላይ እየተመለከተ፤ ቃላቸውን ተገደው እየሰጡ እንደሆነ እያወቀ፤ በፈቃደኛነት የሰጡት ቃል ነው እያለ ምስክርነቱን በመስጠት የመርማሪዎቹን ህገ ወጥ ሰነድ ህጋዊ በማድረግ የመርማሪዎቹን ስራ እንዲያቀል የተመደበ ዳኛም ነበር። የእነዚህን ጨካኝ መርማሪዎችና የዳኛውን ስም ዝርዝር በዘገባው መጨረሻ እናቀርባለን።

## መ)12ኛ ተከሳሽ ኮሎኔል ፋንታሁን ሙሃባ ሙፍቲ

ይህ እስረኛ የተያዘው ሚያዝያ 16 ትግራይ ክልል ምእራብ ዞን ሽሬ ማእከላዊ እዝ ካምፕ ውስጥ ነው። ቢሮው ውስጥ ተቀምጦ ስራውን እየሰራ በነበረበት ወቅት ነበር ክብሪት በሚባል ቅጽል ስሙ በሚታወቀው በኮሎኔል ደሳለኝ ወደ አስተዳደር ቢሮ ተጠርቶ በፈቃዱ ሄዶ ነው እጅ ወደላይ የተባለው። ሚያዚያ 22 2001 አ. ም

ማእከላዊ ምርመራ ሲደርስ ከመንገድ ድካምና በፊቱ ላይ ከሚነበበው ጭንቀት በስተቀር እንደሌሎቹ ከሌሎች ቦታዎች እንደመጡት እስረኞች ፊት ለፊት የሚታይ የአካል ጉዳት አልነበረበትም። በኮሎኔል ፋንታሁን ላይ ቅጥቀጣ የተጀመረው ሚያዝያ 23 2001 ኢ.ም አራዳ ፍርድ ቤት ቀርቦ ለተከሰሰበት ክስ ቃሉን እንዲሰጥ ሲጠየቅ ክሱ ሁሉ ሃሰት ነው ብሎ መልስ በሰጠበት እለት ምሽት ነው። ከምሽቱ አራት ሰአት ላይ በጨለማ አይኑን በጨርቅ ተሸፍኖና እጁን በካቴና ታስሮ እንደበግ እየተጎተተ ተወሰደ። በዛን እለት ለማታው የምርመራ ስራ መርማሪዎች ቁጥራቸው በዛ ብሎ ተመደበ። ኮሎኔሉ ጥጋበኛ እንደሆነና ጥጋቡን ማስተንፈስ እንደሚገባ መመሪያ ተሰጥቷቸው ነው አምስት መርማሪዎች የተመደቡለት። የሚገባው ቋንቋ ዱላ ነውና በሚገባው ቋንቋ አናግሩት የሚለው መመሪያ የተሰጠው በወቅቱ የማእከላዊ ምርመራ ዋና ሃላፊ በነበረው ታደሰ መሰረት በተባለው የለየለት ጨካኝና ዘረኛ የሆነ የትግራይ ተወላጅ የወያኔ ባለስልጣን ነው። ኮሎኔል ፋንታሁን ማእከላዊ ምርምራ ካሳለፉቸው በርካታ ምሽቶች ውስጥ አብዛኛው እስረኛ ሲተኛ እርሱ ሲሰቀል፣ ሲዘቀዘቅ፣ ሲገረፍ በዚህም ምድር ላይ ሰው ይችለዋል ተብሎ የማይገመት ስቃይ ሲወርድበት ነበር። ኮሎኔሉ ላይ በድብደባ የደረሰበት ጉዳት ከፍተኛ በመሆኑ እዛው እስር ቤት ውስጥ እያከሙ ይደበድቡት ነበር። በመጨረሻም እርሱም እንደሌሎቹ እስረኞች መርማሪዎቹ የፈለጉትን ፈርሞ ከአካላዊ ስቃይ ተገላግሏል።

ሠ) 22ኛ ተከሳሽ ወ/ሮ እማዋይሽ አለሙ

በማእከላዊ ምርመራ የተመደቡ ገራፊዎች እናትና እህት የሌላቸው ይመስል በዚች የሶስት ልጆች እናትና የአንድ ልጅ አያት ለመሆን በበቃች ሴት ላይ የፈጸሙት ግፍ እጅግ ዘግናኝ ነው። እንደሌሎቹ ግፉ በእማዋይሽ ላይ የሚፈጸመው ሌሊት ላይ ነው። እንደሌሎቹ አይኗ በጨርቅ ተሸፍኖ እጇ በካቴና ታስሮ ነበር ለምርመራ የምትወሰደው። እየሰቀሉ የውስጥ እግሯን እጆቹዋና ታፋዋን መቀመጫዋን ጀርባዋን በቃላት ለመግለጽ በሚቸግር ጭካኔ ገርፈዋታል። መርማሪዎቹ የሰዎችን ስም እየጠሩና ፎቶግራፍ እያሳዩ ከነዚህ ሰዎች ጋር ተሰብስበሻል፣ ታውቂያቸዋለሽ ይህን እመኚ በነሱ ላይ ለመመስከር እሺ በይን እያሉ ነበር እማዋይሽን የሚገርፏት።

በእማዋይሽ ላይ ከደረሰው አሰቃቂ ግርፋት ግን ልብሷን አስወልቀው ጡቷ እስከሚደማ ድረስ በኤሌክትሪክ ገመድ የገረፏት መሆኑ ነው። ይህች ሴት በጡቷ ላይ የደረሰባት ግርፋት የቀሰቀሰው ስቃይ እና ህመም ወደ ቃሊቲ ወህኒ ቤት ከወረደች በኋላም አልቆመም። የምትኖረው ስቃይ ማስታገሻ ኪኒን እየዋጠች እንደሆነ ከማረሚያ ቤቱ ያሰባሰብነው መረጃ ያሳያል። ወ/ሮ እማዋይሽም ስቃዩን ለማስቆም ገራፊዎቿ የፈለጉትን ፈርማለች።

ረ) 36ኛ ተከሳሽ አቶ ጌቱ ወርቁ

አቶ ጌቱ ወርቁ ከሌሎቹ እስረኛ የሚለየው አማራ አለመሆኑ ነው። የዶክተር ብርሃኑ የቅርብ ዘመድ ነው። በማእከላዊ ምርመራ በእዚህ እስረኛ ላይ የተያዘ መረጃ የለም። ክሱ ግን ከሌሎች ተከሳሾች ጋር በመሆን የሽብር ስራ ለመስራት ማሴር ነው። ይህ እስረኛ እንደሌሎቹ ሁሉ ተመሳሳይ ቅጥቀጣ ተፈጽሞበታል። ከሌሎቹ ለየት የሚያደርገው ከብዙ ድብደባ በሁዋላ ተዝለፍልፎ በወደቀበት ወቅት ገራፊዎቹ ከወደቀበት አንስተው በካቴና በታሰረው እጁ ለ19 ሰአታት የሰቀሉት መሆኑ ነው። አዎን "አንድ ሰው እንዴት ለ19 ሰአት ይሰቀላል?" ትሉ ይሆናል። ይህ የተጋነነ ወይም የተሳሳተ መረጃ አይደለም። የአቶ ጌቱ መርማሪዎች ሌሊት ሲገርፉት ቆይተው ምንም ማግኘት ሳይችሉ ሲቀሩ በዛው ምሽት ሰቅለውት በሩን ዘግተው ወጥተው ሄደዋል። በማግስቱ ከሰአት በኋላ ነው በሩን ከፍተው አቶ ጌቱን ከሰቀሉበት ያወረዱት። ይህ እስረኛ በተሰቀለበት ቦታ እጁ በካቴናው ተቀርድዶ ይፈሰው የነበረው ደም ወለሉን ሞልቶት እንደነበር መረጃ አሰባስበናል። አቶ ጌቱ የደረሰበት ስቃይ እጅግ አሰቃቂና ከፍተኛ ጉዳት ያስከተለበት በመሆኑ ወደ ሽንት ቤት መሄድም ሆነ ሽንት ቤት መቀመጥ ከማይችልበት ደረጃ ላይ ደርሶ ነበር። ከዚህም የተነሳ የእስር ባልደረቦቹ በሚውሉበትና በሚተኙበት ክፍል በባልዲ ላይ በሰው ተደግፎ እየተቀመጠ እዛው ክፍል ውስጥ ይጸዳዳ ነበር። አቶ ጌቱም በመጨረሻ መርማሪዎቹ የፈለጉትን ፈርሞ ግርፋቱ እንዲቆም አድርጓል።

ሰ) 6ኛ ተከሳሽ ሌ/ኮ አበረ አሰፋ

ሌ/ኮ አበረ አሰፋ የተያዘው ሚያዚያ 21 ሃረር ከተማ ውስጥ ነው። ከሁለት ከፍተኛ መኮንኖች ጋር ሚያዘያ 23 ቀን ከቀኑ 6 ሰአት ሶስቱም መኮንኖች ማእከላዊ ምርመራ ሲገቡ እጃቸው በካቴና ከመታሰሩና የለበሱት ልብስ የቆሸሸ ከመምሰሉ በስተቀር የሚታይባቸው የአካል ጉዳት ወይም ጭንቀት አልነበረም። ሶስቱም ታሳሪዎች ቅዳሜ ሚያዝያ 24 2001 ኢ.ም እንደተለመደው አራዳ 1ኛ ፍርድ ቤት ቀርበው የእምነት ክህደት ቃላቸውን ተጠየቁ። የቀረበብን መንግስት የመገልበጥ ሽብር የመፍጠር ክስ ሃሰት ነው ብለው አስተባበሉ። ፖሊስ ማስረጃዬን ለማጠናቀር ታሳሪዎቹ በእስር እንዲቆዩ የግዜ ቀጠሮ ይሰጠኝ በማለት በድንቁርናዋና በታማኝነቷ ለተሾመችው ታሪኳ ለተባለችው የኢህአዴግ አባልና የውሸት ዳኛ ጥያቄ አቀረበ። ሁሌም እንደሚሆነው የፖሊስን ጥያቄ በተለይ በእንዲህ አይነቱ ከፖለቲካ ጋር በተያያዘ ጉዳይ ውድቅ የማድረግ ፍላጎትም ነጻነትም የሌላቸው ዳኞች እንደሚያደርጉት ሁሉ ታሪኳም ተከሳሾቹ በስር ቆይተው ምርመራ ይደረግ የሚል ውሳኔ አስተላለፈች። ታሪኳም ሆነች ሌሎችም ተመሳሳይ ውሳኔ የሚሰጡት የወያኔ ዳኞች በሙሉ ለፖሊስ የመረጃ ማሰባሰቢያ ቀጠሮ ቀን ሲያራዝሙ ፖሊስ ምን እንደሚሰራበት ጠንቅቀው ያውቃሉ። የውሸት ምስክርና ማስረጃ ማሰባሰቢያ ግዜ እየሰጡ እንደሆነ ያውቁታል። ታሳሪዎች ራሳቸውን ወንጀለኛ የሚያደርግ ቃል በዱላና በግርፋት እንዲሰጡ ለማድረግ መርማሪዎች የሚፈልጉትን ግዜ እየፈቀዱ እንደሆነ ያውቁታል። እነዚህ ዳኞች ከገራፊዎቹ ጋር ባንድ ክፍል ውስጥ ተገኝተው እስረኞች በጃቸው አይግረፉ እንጂ በእስረኛ ላይ የሚካሄደውን ሰቆቃ እያወቁ ፈቃድ የሚሰጡ ከገራፊዎቹም በላይ በምድር በወንጀለኛነት፣ በሰማይ በሃጢያተኛነት አስከፊ ቅጣት ሊቀጡ የሚገባቸው ናቸው። ይህች የአራዳ ፍርድ ቤት አንደኛ ችሎት ዳኛ ሌ/ኮ አበረ ታስሮ ምርመራ ይቀጥል ብላ በወሰነች በሁለተኛው ቀን ሚያዚያ 25 2001 ከምሽቱ 2. 30 ላይ በሌ/ኮ አበረ ላይ ምርመራው ተጀመረ። በመጀመሪያ ማስፈራራት ቀጥሎ በወያኔዎች የተለመደውን በዘር ላይ የተመሰረተ አማራነትን የሚያንቋሽሽ ስድብ እና ድንፋታ ቀጠለ። ሌ/ኮ አበረን የመረመሩት መርማሪዎች የሌላ ዘር ያልተቀላቀለባቸው በታደሰ መሰረት የተመደቡ የትግራይ ተወላጆች ነበሩ። በኮ/ል አበረ ላይ ያለምንም ማመንታት የወረደው ለከት የሌለው ብልግና የተቀላቀለበት እና የለየለት ጸረ -አማራ የሆነ ስድብ ገራፊዎቹ በሙሉ የትግራይ

ተወላጆች በመሆናቸውና የተናገሩት የትም አይሰማም ከሚል የርስ በርስ መተማመን የመጣ ነበር። ያልገባቸው ነገር ቢኖር እነሱ በደም ፍላት ከሚያጎርፉት ስድብ መሃል የተወሰነው እነሱ ሰው ከሚገርፉበት ክፍል አልፎ ውጭ ለነበሩ ለሌሎች ሰዎች ጆሮ ይደርስ እንደነበር ነው። ይህንን የመሰለው ስድብ በዘረኛ ገራፊዎች የተለመደ ለመሆኑ ከተከሳሾቹ አንዱ የሆኑት ጀነራል አሳምነው ጽጌ ራሳቸው በወያኔ ችሎት ላይ ቃል በቃል ለዳኞቹ ደግመውታል። እነዚህ ዘረኞች፣ "አሁን በእንዲህ አይነቱ ሽንታም አማራ ነው በስንት ቆራጥ የትግራይ ጀግና ልጆች ያመጣነው ስርአት የሚናደው? አንተን ብቻ አይደለም ዘርማንዘርህን ቀሚስ አስለብሰን የወጥ ቤታችን ሰራተኛ አድርገን እንገዛዋለን" ይህን የመሰሉ ጸያፍና መዘዛቸውን በውል የማይረዱትን ስድብ ነበር አበረን ተሻግረው በአማራ ህዝብ ላይ ሲያወርዱ የነበረው። በማእከላዊ ምርመራ እንዲህ አይነቱ የወያኔ የዘረኛነት ብልግና በእነዚህ ዘረኞች እጅ በገባ ከየትኛውም ዘር በመጣ ታሳሪ ላይ የሚፈጸም ነው። እነዚህ ሰዎችና አለቃቸው መለስ ዜናዊ ህዝብን የብሄር ብሄረሰብ መብት እያሉ እያጭበረበሩ በሆዳቸው ግን አፍነው የያዙት ክርፋቱ እስከአድዋ የሚደርስ በሃገሪቱ ለሚገኙ ዘሮች በሙሉ ያላቸው ንቀት እንደሆነ በማእከላዊ ታስሮ በነዚህ መርማሪዎች እጅ የወደቀ የየትኛውም ብሄረሰብ ተወላጅ ያውቀዋል። ይህ እጅግ የሚያስደነግጥ ነገር ነው። ከስድብ በኋላ በኮሎኔል አበረ ላይ የወረደው የዱላና ጥፊ መዓት ነው። "ህገ መንግስቱን ለመናድ ሰው ስታደራጅ ነበር፤ እመን"ሲሉት "ህገመንግስት ለመናድ ሰው አላደራጀሁም፤ የተያዝኩት ከንግግራችሁም እንደምሰማው ለአማራነቴ ባላችሁ ጥላቻ ነው። የዘረኛ የጥቃት ኢላማ እንጂ ወንጀለኛ አይደለሁም" አላቸው። የኢህዴን መስራችና አሁን የብአዴን ማእከላዊ ኮሚቴ አባላት ሆነው መንግስት እየመሩ ነው የሚሏቸውን ሰዎችና ከፍተኛ መኮንኖች ስም እየጠሩ "አይዟችሁ ግፋበት ይሏችሁ ነበር፣ እንዳይጋለጡም አንተ ብቻ እንድታገኛቸው ይደረግ ነበር፤ ሁሉንም እናውቃለን። ተናገር!!!" እየተባለ በየምሽቱ ለበርካታ ቀናት ኮሎኔል አበረ ከሰውነት ተራ እስኪወጣ በዘረኞች ተቀጠቀጠ:: ኮሎኔል አበረ ከእነዚህ የስቃይ ምሽቶች በአንዱ እግሩን ወደላይ ተገልብጦ በሚገረፍበት ወቅት በዱላ ብዛት የግራ እግሩ አውራ ጣት ጥፍሩ ከጣቱ ተገንጥሎ ተንጠለጠለ። ከደብዳቤዎቹ አንዱ "ይህን ትምክህተኛ አማራ ትምክህቱን የማወጣለት እኔ ነኝ" በማለት ጥፍሩ ተገንጥሎ

በተንጠለው ጣት ላይ በጫማው ቆመበት። በዚህ ስቃይ የተነሳ ራሱን ሲስት ዱላው ቆመ። በማግስቱ ጠዋት እዛው እስር ቤት ውስጥ ባለው ሃኪም ቤት ለህክምና ተወስዶ ያየችው ሃኪም በምታየው ብታዝንም "እኔ ምን ማድረግ እችላለሁ የእንጀራ ጉዳይ ነው" ብቻ ነበር ማለት የቻለችው። በድብደባው ብዛት ኮሎኔል አበረ የሚንቀሳቀሰው፣ ሽንት ቤት የሚሄደው በሰው ተደግፎ ነበር። ሽንት ቤትም ራሱን ችሎ መቀመጥ ባለመቻሉ ብሎኬት ተደርድሮለት ነበር የሚቀመጠው። በመጨረሻም ኮሎኔሉን ስቃይ ፈታው። እንደሌሎች ወንድሞቹና እህቶቹ የፈለጋችሁትን እፈርማለሁ አላቸው። የርሱ ፋይል በዚህ ተዘጋ።

## ሸ) 13ኛ ተከሳሽ ሻለቃ መሰከረ ካሳ

ሻለቃ መሰከረ ካሳ ከሃረር ከነኮሎኔል አበረ ጋር ተይዞ የመጣ ነው ። በተመሳሳይ የእስርና የድብደባ ሂደት አልፏል። አይኑ እየተሸፈነ እጁ በካቴና ታስሮ በቀን በትንሹ ለስድስት ሰአታት ካንድ ሳምንት በላይ የአካልና የመንፈስ ሰቆቃ ተፈጽሞበታል። ክሱም፣ የመርማሪዎቹ እብሪት፣ በዘረኝነታቸው የሚያቀርቡለት ጥያቄዎች ከኮሎኔል አበረ ጋር ተመሳሳይነት ነበረው። በመጨረሻም ሻለቃው መርማሪዎቹ የፈለጉትን ፈርሞ ስቃዩን ማስቆም ነበረበት። ፈርሞ ከአካላዊ ስቃይ ተገላገለ።

## ቀ) 31ኛ ተከሳሽ ምክትል ሳጅን ይበልጣል ብርሃኑ

ይህ የፌደራል ፖሊስ ባልደረባ በተመሳሳይ የእስርና የስቃይ ሂደት አልፏል። መርማሪዎቹ ም/ሳጅን ይበልጣልን ከመፈንቅለ _መንግስቱ እቅድ አውጭዎች ሳይሆን ከፈጻሚዎቹ ጎራ ነው የመደቡት። የደረሰበት ሰቆቃም ማንን እንዲገድል፣ ሽብሩን ያቀነባበሩት ሰዎች እንዳዘዙት እንዲናገርና መርማሪዎቹ አቀናባሪዎች ባሏቸው ሰዎች ላይ እንዲመሰክር ነበር። በጣም የሚያሳዝነው የወያኔ መርማሪዎች በራሳቸው አመለካከት ዝቅተኛ ባሏቸው ሰዎች ላይ የሚያሳዩት ብልግናና ጭካኔ በሌሎቹ ታሳሪዎች ላይ ካሳዩት ጭካኔ የተለየ መሆኑ ነው። ሁሉም እስረኞች ተሰቃይተዋል ነገር ግን እንደ ምክትል ሳጅን ይበልጣል፣ እንደ 32ኛው ተከሳሽ ም/ሳጅን የሽዋስ ምትኩ፣ እንደ 33ኛ ተከሳሽ ሳጅን ውድነህ ተመስገን እንደ 28ኛ ተከሳሽ ሳጅን

አመራር ባያብል ግን ለሳምንታት ያላቋረጠ የአካልና የመንፈስ ሰቆቃ የተፈጸመበት እስረኛ የለም። ሰላሳ አንደኛው ተከሳሽ በነጀነራል ተፈራ ማሞና በሌሎች ከፍተኛ መኮንኖችና ሌሎችም መርማሪዎቹ እንዲወነጀሉላቸው በፈለጓቸው ሰዎች ላይ ምስክር እንዲሆን ነበር የተፈለገው። መርማሪዎቹ ማቅረብ የሚችሉት ትልቁ መረጃ የሰው ምስክርነት ስለነበር እነዚህን ዝቅተኛ ማእረግ ያላቸውን የፌደራል ፖሊስ አባላት በማሰቃየት በታሰሩት ላይ የምስክርነት ቃላቸውን ሰጥተዋል ብለው ማቅረብ ነበረባቸው። በማእከላዊ ምርመራ ውስጥ ባሰባሰብነው መረጃ መሰረት አንደኛው ተከሳሽ ጀነራል ተፈራ ማሞ ከጥያቄ በስተቀር በሌሎች እስረኞች ላይ የተፈጸመው ዱላና ቅጥቀጣ በሳቸው ላይ መፈጸሙን የሚያሳይ መረጃ ማግኘት አልቻልንም። ነገር ግን በጀነራሉ ላይ እንዲመሰክሩ በርካታ እስረኞች ከፍተኛ ሰቆቃ ተፈጽሞባቸዋል። የምክትል ሳጅን ይበልጣል ሰቆቃ የከፋ የሆነው በዚህ ምክንያት ነበር። ምክትል/ ሳጅን ይበልጣል ሁሉም እስረኛ የደረሰበት ስቃይ ደርሶበታል። ከሌሎቹ ለየት የሚያደርገው ስቃይ ግንቦት 4 ቀን 2001አ. ም ከምሽቱ 3 ሰአት እንደተለመደው አይኑ ተሸፍኖ እጁን በካቴና ታስሮ እርሱ ወደ ግርፋት የሚወሰድ መስሎት በነበረበት ምሽት የተፈጸመ ነው። በዛ ምሽት ሳጅን ይበልጣል እንደ በግ እየተጎተተ የተወሰደው ወደ መገረፊያ ክፍል ሳይሆን ወደ አንዲት መኪና ነው። በመኪናዋ ውስጥ እንዲገባ ከተደረገ በኋላ እዛው አዲስ አበባ አካባቢ ወደሚገኝ ዛፍ የበዛበት ስፍራ ተወሰደ። መርማሪዎቹ ከላሽናቸውንና ሽጉጣቸውን እያቀባበሉ "ተገድለህ እዚህ ጫካ ውስጥ እንድትጣል ተፈርዶብሃል። ለቤተሰቦችህ የምትናዘዘው ነገር ካለህ ተናዘዝ" እያሉ ማለቂያ የሌለው የመንፈስ ስቃይ ፈጽመውበታል። መርማሪዎቹ ለመግደል የሚመች ቦታ የሚያማርጡ በማስመሰል እስረኛው እንዲሰማ እያደረጉ እየተነጋገሩ በእስረኛው ላይ ያደረሱትን ጭንቀት "አሸናነው" በሚል ቃል ጀብዳቸውን በማእከላዊ ምርመራ ግቢ ውስጥ ያለምንም ፍርሃት ሲያስተጋቡት ነበር። እዛ ጫካ ውስጥ ም/ሳጅን ይበልጣል መሬቱ ላይ በደረቱ እንዲተኛ ተደርጎ መርማሪዎቹ እርስ በርሳቸው በለው በለው ሲባባሉ ሊሞት የመሰለው ሳጅን ያሰማ የነበረውን ልመናና ተማጽኖ መርማሪዎቹ እንደ ትልቅ ቀልድ ነበር እርስ በርሳቸው የሚያወሩት:: መሬት ላይ ለብዙ ግዜ አስተኝተውት በጥይት እንደሚገድሉት እያሾፉ፣ በእንግሊዝ አስልጣኞቻቸው የተነገራቸውን የጥሩና የመጥፎ ፖሊስ ጨዋታ አንዱ

“ግደለው”ሌላው “ይህ እኮ ምስኪን ደሃ ነው። ምን ያውቃል መገደል ያለባቸው ለዚህ ያበቁት አዛገሮቹ ናቸው” እያሉ የሰሩትን ድራማ እየሳቁ በምርመራ ማእከሉ ቡና ቤት ሲያወሩት ብዙ ሰው ሰምቷቸዋል። እዛ ጫካ ውስጥ ይበልጣል በሽጉጥና በክላሽ ሰደፍ መመታቱ፣ አይኑን በጨርቅ ታስሮ ወደፊት ሂድ እየተባለ መረገጡ ከዛፍ ጋር ሲጋጭ ሆዳቸውን እስከሚያማቸው ይስቁ እንደነበር መርማሪዎቹ እርስ በርሳቸው በሚያደርጉት ቀልድ ይገለጽ ነበር። ባገኘነው መረጃ መሰረት መርማሪዎቹ ሳጅን ይበልጣልን እዛ ጫካ ውስጥ “ለአንተ ማን ጥይት ያበላሻል እዚሁ በገመድ ዛፍ ላይ ማንጠልጠል ነው” እያሉ የገመድ ሽምቀቆ ባንገቱ አጥልቀው ገመዱን ዛፍ ላይ እየወረወሩ አንገቱ ላይ ገመዱን በማጥበቅና በማላላት ያደረሱበት ስቃይ የሚዘገንን ነበር። ይህ ሁሉ ተፈጽሞበትም ይበልጣል የማውቀው ነገር የለም በማለት በማስቸገሩ መርማሪዎቹ ወደ ማእከላዊ ምርመራ ግቢ መልሰው በአንድ የምርመራ ክፍል አስገብተው የኤሌክትሪክ ገመድ በጥርሱ አስነክሰው የኤሌክትሪክ ሞገድ በመልቀቅ ሌላ አሰቃቂ ሰቆቃ ፈጸሙበት። በኤሌክትሪኩ ግፊት ይበልጣል ነጥሮ መሬት ላይ ተዘረረ ውሃ በላዩ ላይ ቸልሰው “ይበቃል ወይም እንጨምር?” አሉት። እጁን አንስቶ “ይበቃል፤ የምትሉት ሁሉ ትክክል ነው” አላቸው። የይበልጣል ስቃይ ግን በዚህ አላበቃም። መርማሪዎቹ ይበልጣል በርካታ ሰዎችን ወንጀለኛ የሚያደርግ ምስክር እንዲሆንላቸው ፈልገው ስለነበር ግንቦት 6 ቀን 2001 እንደተለመደው በምሽት ለምርመራ ወሰዱት። የሰዎችን ስም ጠርተው እነዚህ የመንግስት ባለስልጣኖችን ግደልና ብር እንሰጥሃለን ያሉት ሰዎችን ስም ጠርቶ ምስክር እንዲሆናቸውና እና እነሱም በነጻ እንደሚለቁት መርማሪዎቹ ነገሩት። ይበልጣል አላደርገውም አለ። ይህን ምላሹን የሰሙ መርማሪዎች መቀመጥም መተኛትም ወደ ማይቻልበት ማእከላዊ ምርመራ ውስጥ ሰዎችን ለማሰቃየት በተሰራ ክፍል ውስጥ ወርውረውት ሄዱ። የዛኑ ምሽት ተመልሰው በመምጣት ድንፋታ በተሞላው ሁኔታ ሌሎች መርማሪዎች እየሰሚቸው “አንተ ደም መጣጭ ነፍሜ እናቃጥልሃለን” በማለት ወደ ሌላ ክፍል እንደበግ እየጎተቱ ወስደው ተጨማሪ ሰቆቃ ፈጸሙበት። የውስጥ ሱሪውን ሳይቀር አስወልቀው ከገረፉት በኋላ በውሃ የተሞላ የሃይላንድ ውሃ መያዣ ላስቲክ እቃ ከብልቱ ጋር አስረው እየጎተቱ ሲቃውና ጩኸቱ ደስታቸውን እንዳይሰርቀው በሌላ ሰውም እንዳይሰማ በገማ ካልሲ አፉን ጠቅጥቀው ሲገርፉት ራሱን ስቶ

ወደቀ። እንደለመዱት ውሃ ቢደፉበትም አልነቃ ያላቸው መርማሪዎች ይበልጣልን ከጠባቂ ፖሊስ ጋር ላስቸኳይ እርዳታ ፖሊስ ሆስፒታል መላካቸውና በፖሊስ ሆስፒታል ጥቂት ቀናት ከታከመ በኋላ ተመልሶ እስከ ግንቦት30 ድረስ ከማንም እስረኛ ጋር ሳይገናኝ መክረሙን ማጣራት ችለናል። በይበልጣል ላይ የደረሰውን ሰቆቃ የሚያውቁ የማእከላዊ ምርመራ ሰራተኞች የሰው ልጅ በቀላሉ እንደማይሞት እጅግ ብዙ የአካልና የመንፈስ ስቃይ መቋቋም እንደሚችል በምሳሌነት የሚጠቅሱት ሰው ሆኗል።

በ) 32ኛ ተከሳሽ ም/ሳጅን የሺዋስ ምትኩ።

ም/ ሳጅን የሺዋስ ምትኩ በተመሳሳይ እንደማንኛውም እስረኛ አይኑ በጨርቅ ተሸፍኖ እጁ በካቴና ታስሮ ከታሰረበት ክፍል እየተወሰደ ለተከታታይ ምሽት መርማሪዎች እየተፈራረቁ ወፌላላ ሰቅለው ውስጥ እግሩን በኮረንቲ ገመድ ሲገርፉት፤ በዱላ በቡጢ ሲነርቱት፤ በጥፊ ጆሮው እስከሚደፈን ሲጠፈጥፉት የነበረ እስረኛ መሆኑን ማረጋገጥ ችለናል።

ተ) 33ኛ ተከሳሽ ሳጅን ውድነህ ተመስገን

ሳጅን ውድነህ ተመስገን የተያዘው ግንቦት5 2001 ኢ.ም ከምሽቱ 12.30 ላይ ነው። ያገኙ ዋና ኢንስፔክተር በርሄ ይባላል። የተያዘው ከሚሰራበት ቦታ ነው። ለግዳጅ ስራ ትፈለጋለህ በሚል መኪናው ውስጥ በርሄ አስገብቶት ነው ወደ ማእከላዊ የወሰደው። ማእከላዊ እንደደረሰ ለተወሰነ ግዜ አንድ ቢሮ ፊት ለፊት በተሰራ በረንዳ ላይ ተቀምጦ ታይቷል። ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ መሳሪያ የያዙ የፌደራል ፖሊሶችና ጥቂት መርማሪዎች ከበርሄ ጋር ተመልሰው መጥተው ሳጅን ውድነህን እጁን በካቴና አስረው አይኑን በጨርቅ ሸፍነው በጠራራ ጸሃይ ሃገር እያያቸውና እየሰማቸው "አንተ ሆዳም አማራ በገንዘብ ተገዝተህ መንግስት ላይ ለመተኮስ ግዳጅ ተቀብለህ ስትዘጋጅ ነው የደረስንብህ" እያሉ እያዳፉ ወሰዱት። የመምሪያው አዛዥ ታደሰ መሰረትና ሌሎች ትግሪኛ ተናጋሪ መርማሪዎች ተዘጋጅተው እሚጠብቁበት ክፍል ውስጥ ወስደው አስገቡት። ዱላው የጀመረው የዛኑ እለት ነበር። ሹሙና በሹሙ ቢሮ የተሰበሰቡት ዘረኞች አማራ ስለሚባለው ዘር የሚችሉትን ሁሉ ባለጌና አዋራጅ

ስድብ ተሳደቡ። ደስ ያላቸው በጥፊ ደስ ያለው በቦክስ ደስ ያለውም በርግጫ ውድነህን ደቆሰ። ምርመራው እንደሚቀጥል ነግረው ወደ መታሰሪያ ክፍል ላኩት። በማግስቱ ከምሽቱ ሁለት ሰአት እስከ ምሽቱ 4 ስአት ለሁለት ሰአት የመቀጥቀጥ ሱሳቸውን ተወጡበት። ግንቦት 7 2001 አ.ም በሳጅን ውድነህ ተመስገን ላይ የደረሰው ሰቆቃ ግን ከሌሎች ቀኖች የተለየ ነበር። የገዛ ካልሲውን ባፉ ጠቅጥቀው የውስጥ ሱሪውን አስወልቀው ብልቱንና የዘር ፍሬውን እንደከብት በመቀጥቀጥ አሰቃይተውታል። እራሱን ስቶ እግዜር እንደፈጠረው እርቃኑን ለብዙ ግዜ ወለሉ ላይ ወድቆ ስለነበር እንዲነቃ ውሃ ሲደፉበት ነበር። ወደ እስር ክፍሉ ሲመለስ በደረሰበት ቅጥቀጣ እጅ እግሩ እና ጭንቅላቱ አብጡዋል። ከአናቱም ደም ይፈስ ነበር። ሽንቱን ለመሽናት ሲሞክር በብልቱ ላይ የሚሰማው ስቃይ አብረውት የታሰሩትን ጭምር ያስለቀሰ፣ በመከራ አምጦ ሲሸናም የሚሸናው ደም ብቻ እንደነበር ለማወቅ ችለናል። ዋናውን የምርመራ ድብደባ ያካሄዱት ግለሰቦች እነማን እንደነበሩ በስም ይታወቃሉ።

## ቸ) 28ኛ ተከሳሽ ዋ/ሳጅን አመራር ባያብል

ዋ/ሳጅን አመራር ባያብል በኮማንደር ወርቁና በዋና ኢንስፔክተር በርሄ በሚመራ ወደ ሰላሳ የሚሆን ሬንጀር ለባሽ እንዲከበብ ተደርጎ በሚሰራበት ቦታ ሚያዝያ 16 ቀን 2001 ተያዘ። እንደሌሎች ሳጅኖችና ምክትል ሳጅኖች የውስጥ ሱሪው ሳይቀር በመርማሪዎች እንዲወልቅ እየተደረገ በሌሎች ላይ የደረሰው ሰቆቃ በሙሉ በማእከላዊ ምርመራ ተፈጽሞበታል። ሳጅን አመራር ባያብል ለ14 ምሽቶች ሳያቋርጥ በየምሽቱ ይህ ነው የማይባል ሰቆቃ ተፈጽሞበታል። በምርመራ ወቅት አንዱ ትግራዋይ መርማሪ "ቆሻሻ፣ ዘረ ቆሻሻ" ብሎ በመሳደብ በጁ ይዞ የነበረውን የሞቀ ሻይ እፊቱ ላይ ደፍቶበታል። ሳጅን አመራር የቀረበበት ክስ "አራት የመንግስት ባለስልጣናትን ለመግደል ተዘጋጅተህ ነበር። ይህንንም መመሪያ የሰጡህን ሰዎች ታውቃቸዋለህ በነሱ ላይ መስክር" የሚል ነበር። የምርመራውና የግርፋቱ አላማ ይህን ክስ እንዲያምን ለማስገደድ ነበር። በሰቆቃ ብዛት መርማሪዎቹ የፈለጉትን ጽፈው እንዲፈርምላቸው አደረጉት።

## ኀ) 20ኛ ተከሳሽ የሽዋስ መንገሻ

ሚያዘያ 19 ከምሽቱ 3 ሰአት አካባቢ በየሸዋስ መንገሻ ላይ የተጀመረውና ለተከታታይ ምሽት የቀጠለው በግርፋት የታጀበ ምርመራ ለዚሁ እስረኛ ስለማእከላዊ ምርመራ ሃይለኛ መስሪያ ቤትነት በተሰጠ መግለጫ ነበር። "እዚህ ገብቶ ሳይለፈልፍ የወጣ ጀግና የለም። ስንቱን ምንም አይበግረኝም ያለን ጥጋበኛ ጫማችንን እየላሰ ማሩኝ እንዲል አድርገናል። አልናገርም ካልክ መሃይም ስለሆንክ በመሃይም ቋንቋ እናናግርሃለን። ጥፍርህ ይነቀላል፤በገመድ ትንጠለጠላለህ፤ በኤሌክትሪክ ትቀልጣለህ" የሚል ማስፈራሪያም ታክሎበት ነበር ምርመራው የጀመረው። የሸዋስ "ሰለሚያወሩት ክስና ጉዳይ የሚያውቀው ነገር እንደሌለ" ሲመልስላቸው መርማሪዎቹ በማስጠንቀቂያቸው የዛቱትን ሰቆቃ በሙሉ በየሸዋስ ላይ ፈጸሙበት። ለሁለት ተከታታይ ቀናት እግርግዳ ላይ በተመታ ምስማር ላይ በካቴና በታሰረ እጁ እያንጠለጠሉ በግሩ ጥፍር ብቻ እንዲቆም እያደረጉ ዘረኛ አዋራጅ ስድብ እየሰደቡ ቀጠቀጡት። "የኛ በላይ ዘለቀ!!!" እያሉ ተሳለቁበት። "ትምክህት ያለቀቀህ አማራ" እያሉ ፊቱ ላይ እየተፉ ዘረኛ ጥላቻቸውን እየገለጹ ለረጅም ሰአታት ራሱን ሲስትባቸው ውሃ እያፈሰሱ ደበደቡት ። በመጨረሻም ስቃዩን መቋቋም ያልቻለው የሺዋስ መርማሪዎቹ የፈለጉትን ቃል ለመስጠት እሺ አላቸው። ጽፈው ያመጡለትን በሙሉ ትክክል ነው ብሎ ፈረመላቸው።

## ነ) 11ኛ ተከሳሽ ሻለቃ አዱኛ አለማየሁ

ይህ ሻለቃ እጁ የተያዘው ሚያዝያ 16 2001 ሲሆን ከሌሎቹ እስረኞች በሁለት ነገር ይለያል። የመጀመሪያው ከባለቤቱና ከአንድ አመት ከ6 ወር ልጁ ጭምር ማእከላዊ ምርመራ የታሰረ መሆኑ ነው። ሁለተኛው በፍርድ ቤት ቆሞ በሚስቱና በራሱ ላይ የተፈጸመውን እጅግ አሰቃቂ ሰቆቃ ክዶ በወያኔ መርማሪዎች "እንፈታሃለን" ድለላ ተታሎ ቃሌን የሰጠሁት ያለምንም ማስገደጃ በፈቃዴ ነው በማለት በጓደኞቹ ላይ መስክሮ የ15 አመት ጽኑ እስራት ተፈርዶበት ወህኒ የወረደ መሆኑ ነው። በማእከላዊ ምርመራ በነበረበት ወቅት ሻለቃ አዱኛ ለመርማሪዎቹ ምስክር ሆኖ ለመቅረብ እስከተስማማበት እለት በባለቤቱ በራሱና በህጻን ልጁ ላይ የተፈጸመበት ኢሰብአዊ ግፍ ግን መነገር የሚገባው ነው። እሱም

ባለቤቱም ሌሊት ሌሊት እጃቸው በካቴና ታስሮ አይናቸው በጨርቅ ተሸፍኖ እየተወሰዱ በአፋቸው ጨርቅ እየተጠቀጠቀ ከፍተኛ ድብደባና ግርፋት ተፈጽሞባቸዋል። የሻለቃ አዱኛን ባለቤት ከታሰረችበት አውጥተው ወስደው ሲገርፏት ህጻን ልጇ እናቷ በታሰረችበት ክፍል ሆና ልብ በሚሰብር ሁኔታ ምርር ብላ ታለቅስ ነበር። አብረዋት የታሰሩ ሌሎች ሴት እስረኞች ህጻኗን አባብለው ለቅሶዋን ማስቆም ስለማይችሉ እንዲህ አይነቱ መከራ ውስጥ ለወደቁት ህጻን ልጅ እና እናት እነሱም እንደ ህጻኒቱ ከማልቀስ ሌላ የሚያደርጉት አልነበራቸውም። ሻለቃ አዱኛ አለማየሁና ሻለቃ አደፍርስ አሳምነው አቃቤ ህጉ ሌሎችን ለመወንጀል የሚያስችለው ምስክሮች ሆነው በመቅረብ እጅግ አስነዋሪ ድርጊት የፈጸሙ ቢሆንም በተለይ በሻለቃ አዱኛ፣ በባለቤቱና አንድ አመት ከስድስት ወር ባልሞላት ህጻን ልጁ ላይ የወያኔ መንግስት የሰራውን ግፍ የሃገሬም ሆነ የአለም ህብረተሰብ እንዲያውቀው በዚህ ሪፖርት አካትተናቸዋል። ወያኔዎችም በፍርዱ ሂደት በተለይ በአዱኛ ላይ የፈጸሙት ግፍ እንዳይጋለጥባቸው እሱን በመደለል መልሰውም በመክዳት ምስጢሩን የቀበሩት ቢመስላቸው እውነቱ ይኸው መውጣቱ አልቀረም።

ኘ) 21ኛ ተከሳሽ መንግስቱ አበበ

አቶ መንግስቱ አበበ ከሰኔ 16 ጀምሮ ለ45 ቀናት በማእከላዊ ምርመራ እስርቤት ስቃዩን አይቷል። ይህ ወጣት ኤንጂንየር የግንቦት 7 እስረኞች በሚል ስም ከተያዙት በጣም ጥቂት ሲቪሎች መሃከል አንዱ ነው። ለእስር በተዳረገበት ወቅት እንደሱው ኤንጂነር የሆነችው ባለቤቱ ለከፍተኛ ትምህርት ውጭ ተልካ የሶስት አመት እድሜ ያልሞላትን ሴት ልጃቸውን መንግስቱ ብቻውን አሳዳጊ ነበር። ከወፌላላ አንስቶ ማንኛውንም የግርፋት አይነት መርማሪዎቹ ሞክረውበታል። በብልቱ ላይ ባረፈበት ዱላ የተነሳ ለሶስት ቀናት ደም ሸንቷል። ከአንድ ሳምንት በላይ በራሱ መነሳትም መቀመጥም ባለመቻሉ ለማናቸውም እንቅስቃሴ የሌሎች እስረኞች ድጋፍ ያስፈልገው ነበር። ተመሳሳይ ጉዳት እንደደረሰባቸው ሌሎች እስረኞች ሽንት ቤት ቁጢጥ ብሎ መቀመጥ ባለመቻሉ ብሎኬት ተደርድሮና እዛ ላይ ተቀምጦ ነበር የሚጸዳዳው። መንግስቱ ስለደረሰበት ሰቆቃ በራሱ በወያኔ ፍርድ ቤት በቆራጥነትነትና

እልኸኝነት አንስቶት መርማሪዎቹ የካዱት ጉዳይ ነው። መርማሪዎች ቢክዱትም መንግስቱ አበበ አብረውት በአንድ ክፍል ከሱ ጋር ታስረው፣ እንደሱ ማታ ማታ ለጥያቄ አይናቸውን በጨርቅ እጃቸው በካቴና እየታሰረ ከዘጠኝ ግዜ በላይ ተወስደው በምርመራ ስም ሲዋረዱና ሲሰቃዩ የነበሩትን የ83 አመት አረጋዊ (የግንቦት 7 አመራር ናቸው የሚባሉት የአቶ አንዳርጋቸው ጽጌን አባት) አቶ ጽጌ ሃብተማሪያምን በምስክርነት ጠርቶ እርሳቸውም በራሱ በወያኔ ፍርድ ቤት ቆመው መንግስቱ ክፉኛ ለመደብደቡ ምስክርነታቸውን የሰጡበት ጉዳይ ነው። በመንግስቱ ላይ የተፈጸመው ድብደባና ግርፋት ወደ አደባባይ መውጣቱ መርማሪዎቹ በሌሎች እስረኞች ላይ የፈጸሙትን ግፍ ያፈነዳዋል የሚል ስጋት ያደረባቸው የመንግስት ባለስልጣናት አቶ ጽጌ ሃብተማሪያም የመንግስቱ አበበ ምስክር እንዳይሆኑ ለማግባባት ሞክረው ሳይሳካላቸው ቀርቷል። “በእርስዎ የእስር ጉዳይ ለመደራደር ፈቃደኛ ነን” ለሚለው የአሳሪዎቻቸውን ማጭበርበሪያና ተጽእኖ ” “በዚህ እድሜዬ ያየሁትን እውነት ካልተናገርኩ መቼ ልናገር ነው? እናንተ የፈለጋችሁትን አድርጉ” የሚል ምላሽ ለአሳሪዎቻቸው በመስጠት ስለ መንግስቱ አበበ መደብደብ የምስክርነት ቃላቸውን ሰጡ። እኝህ ከእድሜያቸው መርዘም ጋር አቅማቸው የደከመ፤ አሳሳቢ የልብ ድካምና የስኳር በሽታ ያለባቸው አዛውንት ለመንግስቱ ምስክር በመሆናቸው በወያኔ ዘረኛ መርማሪዎች አፍ “የተረገመ ሽማግሌ” የሚል ስም አሰጥቷቸው በዚህ እድሜያቸው እድሜ ልክ ተፈርዶባቸው ወህኒ ወርደዋል:: መንግስቱ አበበ በግርፋትና በድብደባ ተገዶ ቃሉን እንደሰጠ፣ የሰጠው ቃልም ደብዳቢዎቹ ጽፈው የሰጡት የራሳቸው ቃል እንደሆነ የ83 አመት የእድሜ ባለጸጋ ምስክርነት ቢያቀርብም ዳኞቹ አልተቀበሉትም። ፍርድ ቤቱ “ከአቶ ጽጌ ምስክርነት ይበልጥ መንግስቱ አበበ የሰጠው ቃል ያለምንም ማስገደጃ መሆኑን አረጋግጣለሁ የሚል ፊርማውንና ስሙን መርማሪዎቹ ባዘጋጁት ሰነድ ግርጌ ያሰፈረውን የዳኛ ሽምሱ ሲርጋጋን ቃል አክብደን እናያለን። የመርማሪዎቹ ድብደባ የነመንግስቱና የነአቶ ጽጌ የፈጠራ ድርሰት ነው በማለት” ደመደመ። የመንግስቱ አበበ ፍትህ የማግኘት ጥረት መና ሆኖ ቀረ። ፍርድ ቤቱ የወንጀለኛ መቅጫ ህግ ስነ ስርአት ቁጥር 35ን እየጠቀሰ እነ መንግስቱ አበበ በዳኛ ሽምሱ ፊት ቃላችንን በፈቃደኛነት ነው የሰጠነው ያሉበትን ሰነድ እያመላከተ የሞት እና የእድሜ ልክ ጽኑ እስራትን በስረኞቹ ላይ ወሰነ። እነዚህ ጨካኝ

ገራፊዎቹ እነማን ናቸው? በዚህ የፍትህ ውርጃ በሆነ እኩይ ሴራ ውስጥ የዳኛ ሽምሱ ሚና ምንድን ነበር? የሚቀጥለው ትኩረታችን በነዚህ ጉዳዮች ላይ ይሆናል።

## 7. አስገራፊና ገራፊ፤

የሃገራችንን ጉዳይ አሳሳቢ የሚያደርገው ሰራዊቱን ደህንነቱን መደበኛውን ፖሊስና የፌደራል ፖሊሱን እንዲሁም በወንጀል ምርመራና ሌሎችንም የስልጣን ዋልታ የሆኑትን ወሳኝ የሃገሪቱን ተቋማት ሙሉ በሙሉ በበላይነት የተቆጣጠሩት፤ የፈለጉትን ወንጀል ቢፈጽሙ፤ እንዳሻቸው ቢገድሉ፣ ቢያስሩ፣ ቢቀጠቅጡ ጠያቂ የሌላቸው ከአንድ ዘር የተውጣጡ የትግራይ ተወላጆች መሆናቸው ነው። ይህ በዘር የተደራጀ መዋቅር ዛሬ በሃገራችን የሚታየውን ፈጽሞ በዚህ ባለንበት ዘመን ሊፈጸም ይችላል ብለን ለማንገምተው በኢትዮጵያውያን ላይ ለሚፈጸም ጭካኔና ግፍ ዋናው ምክንያት ነው። በዘረኛነት በሽታ ለተለከፈ ሰው ከሌላ ዘር የሚመጣን ሰው እንደሰው ልጅ አያይም። የሌላ ዘር ህጻናትን እንደህጻን፣ ሴቶችን እንደሴት፣ አረጋውያንን እንደ አረጋዊ ማየት የሚችልበት ሰብአዊ መነጽሩ የጠፋበት ነው። ከሌላ ዘር የሚመጣ ሁሉ ጠላት ነው። የጀርመን ናዚዎች፣ የሩዋንዳ ሁቱዎች ይሁዳውያንና ቱትሲውን ተባይና በረሮ የሚል ከሰውነት ደረጃ የወረደ ስም እየሰጡ እንደፈጁት ሁሉ በወያኔ ዘረኞች አእምሮ ውስጥ ተመሳሳይ አመለካከት እንዳለ ባለፉት 20 አመታት ከተፈጸሙትና ዛሬም እየፈጸሙት ካለው ድርጊቶቻቸው ማየት የምንችለው ነው።

የወያኔ ባለስልጣናት ችግር ዘረኛ አመለካከታቸውን በጀርመንና በሩዋንዳ ደረጃ ለማስፈጸም የሚችሉበት አቅም በጃቸው አለመኖሩ ብቻ ነው። አናሳ መሆናቸው ስፋት ያለው ፍጅት በራሳቸው ለመፈጸም የማያስችላቸው ካልሆነ በስተቀር ዘረኛ የሆነ የጅምላ ፍጅት ለማካሄድ የዘረኛነት እምነት ችግር የለባቸውም። የዚህን ፍንጭ በኦሮሚያ፣ በጋምቤላ፣ በኦጋዴን በሲዳማ በሃዋሳ በጎንደር በጎጃም በአዲስ አበባና በሌሎችም የሀገሪቱ ክልሎችና በመቋዲሾ ህዝብ ላይ ባካያሄዱት ጭፍጨፋ አሳይተውናል። እነዚህ ራሳቸውን የምርጥ ዘር አባላት አድርገው የሚያዩ ባለስልጣናት በስራቸው የሚያዙት ከተለያዩ ብሄሮች የተውጣጣ ቀጥረው የሚያሰሩት የሰው ሃይል አላቸው። ደሞዝተኛው የሃገሪቱን ሃብትና ስልጣን በሙሉ አሰባስበው በጃቸው ያስገቡ ዘረኞች ተቀጣሪና የደሃ ሃገር ዜጋ በመሆኑ ለእንጀራ ሲል

ትእዛዛቸውን ይፈጽማል። ጥቂቶችም ቢሆኑ ከእንጀራ በላይም አልፈው የዘረኞች የቀኝ እጅ ሆነው የሚያገለግሉም አልታጡም። የራሳቸውና ለፈለቁበት ህብረተሰብ ክብር የሌላቸው፣ በገዛ ፈቃዳቸው ለዘረኞች አደግዳጊ የሆኑ የሰው ጎዶሎችንም እናገኛለን። ቀደም ብለን የጠቀስናቸው የብአዴን መሪዎች ለዚህ ጥሩ ምሳሌዎች ናቸው።

በማእከላዊ ምርመራ ውስጥም ያለው ሁኔታ ተመሳሳይ ነው።አዛገሮቹ ሹሞቹና ቁልፍ የሆነውን ስልጣን የያዙት የትግራይ ተወላጆች ናቸው። አስገራፊዎችም እነዚህ ሰዎች ናቸው። አሁን ከቦታው ቢነሳም በግንቦት 7 ስም በተከሰሱትና ከዛም በፊት በኦነግነት፣ በኦብነግነት፣ በቅንጅትነት የታሰሩትን ሰዎች በማእከላዊ ምርመራ ውስጥ እንዲሰቃዩ እንዲገረፉ፣ እንዲሁም ማእከላዊ መምሪያው ከፍተኛ የጭካኔ ማእከል ሆኖ እንዲቀጥል ያደረገው ሰው ታደሰ መሰረት ነው። የታደሰ መሰረት የበላይ ጌታቸው አሰፋ ነው። የጌታቸው አሰፋ ጌታ ደግሞ መለስ ዜናዊ ነው። የሚያስተሳስራቸው መንግስታዊ መዋቅር ሳይሆን ዘረኛ መዋቅር ነው። በዚህ መዋቅር ውስጥ የሚተላለፍ ትእዛዝ የሚተላለፈው በትግርኛ ቋንቋ ነው። በታደሰ መሰረት አስገራፊነትና ከሰውየውና ከበላይ አዛገሮቹ በሚመነጭ ዘረኛ አመለካከት የተነሳ፣ ማእከላዊ ምርመራ ከተራ የምርመራ ጣቢያነቱ ተቀይሮ ሰዎች በዘራቸው የሚሰደቡበት፣ የሚዋረዱበት እና የሚሰቃዩበት ተቋም መሆን በቅቷል። የማእከላዊ መምሪያ አዛዥ ለዚህ ዘረኛ እምነቱ ማስፈጸም እንዲመቸው በወያኔ ድርጅታዊ መዋቅር ስራ ያደራጃቸው በፈለገው ሰአትና ግዜ የፈለገውን ወንጀልና ሃጢያት የሚያስፈጽማቸው በተለያዩ ልዩ ልዩ ጥቅሞች ያቆራኛቸው የትግራይ ተወላጆች የተሰባሰቡበት ልዩ ቡድን አለው። ይህ የዘረኞች መዋቅር በሰራዊቱ፣ በፖሊሱ፣ በደህንነቱ ውስጥ አለ። ይህ መዋቅር በሁሉም የሀገሪቱ ክልል በሁሉም መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋሞች ውስጥ የተዘረጋ ነው።

ዛሬ በኢትዮጵያ ውሰጥ በአደባባይ የኢትዮጵያ መንግስት ተብሎ ከሚታወቀው መንግስት ስር ያለው ምንም ህግ የማይገዛው የዘራፊዎችና የጨካኞች ሌላ ዘረኛ መንግስት አለ። በህዝባዊ ወያኔ ሃርነት ትግራይ ድርጅታዊ መዋቅር የተሳሰሩ አባላት ያሉበት መንግስት ነው። ወያኔ የኢትዮጵያን መንግስት ስልጣን ከተቆጣጠረ ከሃያ አመት በኋላም ስሙን ከትግራይ ነጻ አውጭ ድርጅትነት ወደ ሌላ ስም ያልቀየረው ለቀልድ አይደለም። የትግራይ ነጻ አውጭ የሚል ስም ይዞ ኢትዮጵያ የምትባልን

ሃገር በዘር በተደራጁ ሰዎቹ መቆጣጠሪያው ይህ ዘረኛ ድርጅቱ ስለሆነ ነው። እጅግ ዘግናኝ የሆነው በዘር ላይ ያነጣጠረው በማእከላዊ ምርመራና ከማእከላዊ ምርመራ ውጭ የሚፈጸመው ግፍ በነዚህ በዘር በተደራጁ ሰዎች አማካይነት ነው። ከዘር ትስስርና መጠቃቀም የተነሳ ሚስጥር መጠበቅ በመቻሉ በማእከላዊና በሌሎችም የፌደራል ፖሊስ መስሪያ ቤት ከሚሰሩ አሰቃቂ ግፎች መሃል ለህዝብ ጆሮ የሚበቃው ከአስር እጅ አንዱ ብቻ ነው። ይህም ባብዛኛው የሚገኘው ባካባቢው መረጃ ለማሰባሰብ በቻሉ የሌሎች ብሄር ተወላጆች ጥረት ወይም በደሉ ተፈጽሞብናል በሚሉ ደፋር ሰዎች አማካይነት ነው። አንዳንዴም እንደማንኛውም የሰው ልጅ ከዘራቸው በፊት ሰብእናቸውን በሚያስቀድሙ የራሳቸው የትግራይ ተወላጆችም በኩል ሚስጥሮች ይወጣሉ። አልፎ አልፎም ዘረኛ አዛዦቻቸውን እምቢ በሚሉ የትግራይ ተወላጆች በኩል የሚገኙ መረጃዎች አሉ። ጀነራል ተፈራ ማሞን እንዲደበድብ ትእዛዝ ተሰጥቶት እምቢ በማለቱ ወያኔዎች ከስራው አባረው በመኪና ገጭተው ሰንካላ ያደረጉት የትግራይ ተወላጅ የወያኔ የወህኒ ቤት ሰራተኛ እንዳለም ሪፖርት የማድረግ ግዴታ አለብን። ስሙን ባንጠቅሰው ደስ ባለን ነበር፤ ወያኔዎች እስካሁን ካደረሱበት ስቃይ በላይ ሌላ ስቃይ እንደሚያደርሱበት እናውቃለንና። ሆኖም ግን ስሙን እዚህ ጠቅሰነው ከሚደርስበት ጉዳት ይልቅ ሰብአዊ ድርጊቱን ባናነሳው የሚደርስበት በደል የከፋ ነውና ኤርምያስን እግዜር ይጠብቅህ እንለዋለን። ይህ ሰው የነታደሰ መሰረትንና የዘረኛ ጉዋደኞቻቸውን ዘረኛ ትእዛዝ አልፈጽምም በማለቱ ለኢትዮጵያ ህዝብ በተለይ ደግሞ ለትግራይ ህዝብ የዋለው ውለታ ታላቅነት የሚለካው ወደፊት ነው። ታደሰ መሰረት፣ አለቆቹና ያደራጇቸው ገራፊዎች ግን ቀናቸውን ይቆጥራሉ።

በግንቦት ሰባት ስም የታሰሩትን እስረኞች በመግረፍና በማሰቃየት ስራ እራሱ ታደሰ መሰረት ከሚመኘው ክፋት በላይ በመሄድ "ግዳጃቸውን" የተወጡ መርማሪዎች የስም ዝርዝር እንደሚከተለው ይቀርባል።

1) ዮሃንስ ኢንስፔክተር
2) ተዘራ ቦጋለ ኢንስፔክተር
3) ከተማ ኢንስፔክተር
4) ሰይድ አሊ ኢንስፔክተር
5) ታደሰ አያሌው ኢንስፔክተር
6) ብርሃነ ኢንስፔክተር

7) በለጠ ኢንስፔክተር
8) ገብረ መድህን ኑሬ ኢንስፔክተር
9) ሙሉጌታ ኢንስፔክተር
10) አሰፋ አትኩት (ም/ኢንስፔክተር)

ከእነዚህ ገራፊዎች መሃል በጭካኔያቸው ወደር የሌላቸው ዮሃንስ፣ ከተማ፣ ብርሃኑ እና ተዘራ ናቸው። እነዚህ መርማሪዎች በሰው ስቃይ የሚደሰቱ፣ ለማሰቃየት ያላቸው ትጋት ከአእምሮ በሽተኞች ምድብ የሚያስመድባቸው ናቸው። ዮሃንስ ከተማና ብርሃኑ 31ኛውን ተከሳሽ ጫካ ውስጥ ወስደው ያሰቃዩና በኋላም በብልቱ ላይ ውሃ የሞላ ጠርሙስ አንጠልጥለው ከፍተኛ ስቃይና ሰቆቃ የፈጸሙበት መርማሪዎች ናቸው። በሰላሳ ሶስተኛው ተከሳሽ በሳጅን ውድነህ ተመስገን ላይ የተፈጸመውን ስቆቃ የመሩት መርማሪዎች ሰኢድ አሊና ሙሉጌታ ነበሩ። እንደሌሎቹ መርማሪዎች ብዙ የጭካኔ ድርጊቶች መረጃ ካላገኘንበት ከኢንስፔክተር ገብረመድህን ኑሬ በስተቀር የተቀሩት 9 ኢንስፔክተሮች አብዛኛውን ግዜ 5 እየሆኑ በታሳሪዎቹ እንባና ደም የታጠቡ በስቃያቸው የተደሰቱ፡ እስረኞችን አሰቃይተው፣ ራሳቸው ጽፈው እስረኞቹን አስገድደው ያስፈረሙትን የውሸት ማስረጃ ፍርድ ቤት አቅርበው የሞትና የእድሜ ልክ ውሳኔ ያስወሰኑ ወንጀለኞች ናቸው። እነዚህ አረመኔዎችና ዘረኛ ሹሞቻቸው በማእከላዊ እስር ቤት ውስጥ ባለፉት አመታት ለፈጸሙት ግፍ ፍርዳቸውን እንዲያገኙ ኢትዮጵያውያን ወገኖቻችን መደረግ የሚገባውን ሁሉ እንደምታደርጉ ሙሉ እምነት አለን።

## 8. የገራፊዎቹና የዳኛ ሽምሱ ሲርጋጋ ሴራ

በሃገሪቱ ህግ መሰረት አንድ ግለሰብ በመርማሪ ፊት ቀርቦ የሰጠው የእምነት ወይም የክህደት ቃል ተመርማሪው ያለምንም ጫና ወይም ተጽእኖ የሰጠው ለመሆኑ ተመርማሪው ወይም ተጠርጣሪው ከዳኛ ፊት ቀርቦ በዳኛው ሳይረጋገጥ በማስረጃነት ፍርድ ቤት መቅረብ አይችልም። እንዲህ አይነቱን ማረጋገጫ እንዲሰጥ ወያኔ የመረጠው ዳኛ የታወቀውን የወያኔ ካድሬና ፍትህን በመጣስ ሃገርን ያስለቀሰውን ሽምሱ ሲርጋጋ የተባለውን ዳኛ ነው። ዳኛ ሽምሱ ከማእከላዊ ምርመራ በመርማሪዎች የሚቀርቡለትን እስረኞች ደማቸው እየፈሰሰ፣ ፊታቸው አብጦ፣ መሄድ አቅቷቸው በመርማሪዎች ተደግፈው ሲመጡ እያየና እየተመለከተ፣ እነዚህኑ እስረኞች በመርማሪዎቹ ፊት "ይህ የሰጣችሁት ቃል በፈቃዳችሁ ነው አይደለም?" በማለት ጥያቄ የሚጠይቅ ከዱላ ለመገላገል "አዎን"

ያሉትን "ደግ አድርጋችኋል" ብሎ የሚያመሰግን፣ "ተገደን ነው" ብለው ደፍረው የተናገሩትን "ውሰዱና እንደገና መርምሯቸው" ብሎ መመሪያ የሚሰጥ ከመርማሪዎቹ ጋራ መርፌና ክር ሆኖ ሲሰራ የነበረ፤ በስም ብቻ ዳኛ በተግባር ግን እኩይ ተግባር ፈጻሚ ነበር።

ሽምሱ ከገራፊዎች ጋር ተመሳጥሮ ብዙ ግፍ ፈጽሟል። ከታሳሪዎቹ መሃል አንዳቸውም ሽምሱ ጋር ሲቀርቡ ዳኛ ፊት እንደሚቀርቡ አልተነገራቸውም። ሽምሱ አንድም ቀን ተሳስቶ ዳኛ መሆኑን ለታሳሪዎች አላሳወቀም። አብዛኛዎቹ ታሳሪዎች ከሽምሱ ፊት የሚቀርቡበት እለትና ሰአት ዳኛ የሚሰራበትና ሰአት ጋር የማይገጣጠም ስለነበር ሽምሱን የማእከላዊ ምርመራ ቢሮ ከፍተኛ ባለስልጣን እንጂ ዳኛ ነው ብለው መጠርጠር አልቻሉም። ዳኛ ሽምሱ መርማሪዎች በፈለጉት እለት ሰአትና ቀን ይገኛል። ሚያዝያ 27 ምሽት የነጻነት እና የድል በአል ቀን ሳይቀር የውሸት ችሎት እየተቀመጠ መርማሪዎቹ የፈለጉትን ይፈጽም ነበር። ሽምሱ ሌሊት ሰው ከተኛ በኋላ እንዲሁም በሰንበት እለት ፍርድ ቤት ለመሆኑ ምንም ማመላከቻ በሌለው አንድ ክፍል ውስጥ ከመርማሪዎች ጋር ችሎት እየተቀመጠ በፍትህ ላይ ሲያላግጥ የከረመ የወገንና የሃገር ጠላት ነው ብንል የምናጋንን አይመስለንም። 21ኛ ተከሳሽ መንግስቱ አበበ ደሙን እየዘራ ከሽምሱ ሲርጋጋ ፊት ቀርቦ ለመርማሪዎች የሰጠው ቃል ያለምንም ተጽእኖ እንደሆነ የተጠየቀው በነጻነት በአል ቀን ሚያዝያ 27 ምሽት ነው። ሽምሱም ያለምንም ማስገደድ መንግስቱ አበበ ቃሉን ለመስጠቱ እማኝ ለመሆን ችሎት የተቀመጠው በዚሁ የነጻነት በአል በሚከበርበት እለት ነው። ምን አይነት ነጻነት? እናንተው ፍረዱ።

እኛ ይህንን አስከፊ የግፍ ታሪክ ከብዙ ችግር በኋላ ለእናንተ ለወገኖቻችን አድርሰናል። በዚህም በመጠኑም ቢሆን የዜግነት ድርሻችንን ተወጥተናል ብለን እናምናለን። እናንተ ወገኖቻችን ደግሞ ይህንን ግፍ ለማስቆም የምትችሉትን ሁሉ እንድታደርጉ አደራ እንላለን።